

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በአርባ ቀን ሰዎች እያዩት በመላእክት ምስጋና እንደ ዐረገ ።

# ትንሣኤ



ድንግል ማርያም ሆይ! የዓለም ቤዛ ክርስቶስን ትወልጅልን ዘንድ አንቺን የፈጠረ እግዚአብሔር ይመስገን ።

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር ፶፮ ግንቦት ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ራደ አስረስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐናርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

## ማስታወሻ፡

በትንሣኤ፡ መጽሔት፡ ቁጥር፡54፡በገጽ፡6፡ዜና፡ቤ/ያን፡ውስጥ፡ላይ፡(በ1972.ዓ.ም) የሚለው፡በስህተት፡ስለሆነ፡በ1872.ዓ.ም.ተወለዱ፡ተብሎ፡ይነበብ፡ዘንድ፡እናሳስባለን።

ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፭ |
| ራሱን ያለ ምስክር አልተወም | ፰ |
| ሰዎችና መላእክት እያዩት በምስጋና ዓረገ | ፱ |
| ርክበ ካህናት | ፯ |
| እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ | ፲ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፱ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፲ |
| ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ | ፲፪ |
| የሥላሴ ት ቤት መዋለ ሕፃናት | ፲፭ |
| ልደታ ለቅድስት ማርያም | ፲፯ |
| ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ | ፲፰ |
| ፍልሰተ አጽሙ ለተክለ ሃይማኖት | ፲፱ |
| ወርኃ ግንቦትና ክንቱ አምልኮቱ | ፳ |
| የመጀመሪያው የሙሴ ጽላት ስባሬ | ፳፪ |
| አንዳንድ ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ | ፳፫ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፳፱ |


# ደብዳቤዎች

ይድረስ ለትንሣኤ መጽሔት

ከሁሉ አስቀድሜ የእግዚአብሔር ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

እኔ የዚህን መጽሔት መልእክትና ትምህርት ያየሁትና ያነበብሁት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው ። የሚሰጠው ትምህርት እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ በተለይ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች እጅግ ጠለቅ ያለ ትምህርት እንደሚሰጥ ልገነዘብና ልረዳ ችያለሁ ። በተለይም ከማወቅ በፊት መናገርን ለሚያስቀድሙ ከአጉል ተቺዎች ሃይማኖታችንን ለመንከባከብ የሚደረገው ጥረት በብርቱ መቀጠል እንዳለበት አሳስባለሁ ። እኔም ጫፍ ይዘው ለሚበሩት መጠነኛ ትምህርት ትሠጣለች ብዬ ስለገመትሁ ቦታና ጊዜ ካላችሁ የሚከተለውን መልእክት በደብዳቤዎች ዓምድ እንድታወጡልኝ ልኬአለሁ ።

## " ከመናገር ማወቅ ይቅደም"

አባቶቻችን ካወረሱን ትምህርት አንዱ ነገርን በምሳሌ የማስፈርንና በትንሽ አረፍተ ነገር ብዙ ስሜትን የመግለጽ ትምህርታዊ ምሳሌ ነው በዚህም መሠረት በምሳሌ ከተናገሩት ለመጥቀስ ቢያስፈልግ "ከመናገርህ በፊት አስብ ፡ ከመዝለልህ በፊት ማረፊያህን ተመልከት ፡ አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" ወ.ዘ.ተ. ብለው ጫፍ ይዘን እንዳንበርና ሁሉን ከማድረጋችን በፊት ማሰብና ማወቅ እንዳለብን በምሳሌ እንዳስተማሩን ልንረዳ እንችላለን ።

አንድ ሰው ስለ ሃይማኖትም ሆነ ስሌላ ነገር ለመናገር ከፈለገ አስቀድሞ ለመናገር ስለፈለገው ነገር በደንምብ ማጢንና ጠለቅ አርጎ ማወቅና መረዳት ያስፈልገዋል ። ነገር ግን ሳይረዱና ሳያውቁ የሚናገሩት ነገር ሁሉ ራስን ከስህተት ላይ ከመጣሉም በላይ ዓላማውንና ይዘቱን በሚያውቁት ዘንድ የአላዋቂነት ንግግር መሆኑን ግልጥ አድርጎ ያሳያል ። ከዚህ ሌላ ይህ የለመደ አፍ በሀገር ሁኔታ ላይ ቢሆንም "ሳያረጋግጡ ወሬ ሳይገሉ ጎፈሬ ፡ ድንጋይ ፡ ቢያጉኗት ተመልሳ እናት ፡ የነ ቶሎቶሎ ቤት ግድግዳው ሠንበሌጥ" እንደተባለው አንድን ነገር ሳያውቁና አገላብጠው ሳይመለከቱ እንደተገኘ መሰንዘር በለፈለፉ ይጠፉን ያመጣል ። ስለዚህ ጉዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልዕክቱ እንዲህ ይላል ነገርግን ሌሎችን ደግሞ አስተምርዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላትን በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ ።

ወንድሞቼ ሆይ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአእምሮ የበሰላችሁ ሁኑ ይላል ፩ኛ ቆሮ.፲፬ ፡ ፲፱ - ፳፩ ።" እንግዲህ ይህ ቃል በአእምሮ በስለን እንድንገኝና ከመናገር አስቀድመን እንድረዳ የሚያስገነዝበን ሐዋርያዊ ቃል ነው ። ያም ሆነ ይህ ወደ አላማዬ ልመለስና አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለመመልከት እንደጦር የፈሩት ነገር ግን ለትችት ግንባር ቀደም የሆኑት ሃይማኖት ሰውን አትግደል ይላል የሚለውን ከአሥርቱ ቃላት አንዱ የሆነውን ትዕዛዝ መልኩን በመለወጥ ጠላትህም ቢሆን እንዳትገድል ይላልና ሃይማኖትን መከተል አይገባም የሚሉ ጫፍ ይዘው የሚበሩ በየመንደሩ እጅግ የተሳሳተና በተለይም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ዓላማ የሌለውን የሚያወሩ የማጥላሊያ ዘመቻን የተያያዙት አሉ ። እርግጥ የተሠጠው ሀሳብ ወይም ትችት ትክክለኛና የተጨበጠ ዓላማ ያለው ቢሆን ኑሮ ነገሩን ተቀብለን ከሃይማኖታችን ጎዳና ፈቀቅ ባልን ነበር ። ነገር ግን የሚነገረው ነገር ከሃይማኖታችን ዓላማና ይዘት ፍጹም የራቀና በሃይማኖት ታሪካችንም ውስጥ የማይገኝ ስለሆነ የዚህ ዓይነቱ ንግግር አላዋቂነትን የሚያሳይ ሆኖ ይገኛል ።

ሃይማኖታችን ድንበር ጥሶ ውል አፍርሶ አገርን ለመውረር የሚመጣ ጠላትን እንዳንገድል በፍጹም አይከለክለንም እንዲያውም ቀደም ያሉ የሃይማኖት አባቶችም ሆኑ ክርስቲያኖች የመጣባቸውን ጠላት እንደ አሁን የሥልጣኔ መስክ ባልተከፈተበት መገናኛ በሌለበት ጊዜ አንድ ግንባር ፈጥረው የእግዚአብሔርን ኃይል ተገን በማድረግ በእግራቸው ብዙ በረሃን እየተጓዙ የሀገርን ዳር ድምበር ባለማስደፈርና ጥሶ የመጣውንም አዋርደው በመመለስ ሲታገሉ በማለፍ ሀገራችንን ለእኛ እንዳስረከቡን ከታሪክ እናገኛለን ። ለዚህ ዓላማ ለሀገራቸው ነፃነትና ለሃይማኖታቸው ሲሉ ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ደረታቸውን ለመትረየስ ሰጥተው በሰማዕትነት ያረፉትን አቡነ ጴጥሮስን መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል እሳቸውም የሃይማኖት አባት (መሪ) ሆነው ሳለ የጣሊያን መንግሥት የበላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ተገዢ እንደሆነ ለሕዝብ ስበክ ብሎ በመሣሪያ ቢያስፈራራቸውም ልበ ቆራጥ በመሆናቸው እንኳንስ ሕዝቡን ተገዛ ብዬ ልሰብከው ይቅርና መሬቷ እራሷ አትገዛልህ ብለው ገዝተው እንደሞቱ ከአንድ አንድ አባቶች ልረዳ ችያለሁ ታዲያ ሃይማኖት ለጠላት የተሠናዳ መንገድ ሁኑት ቢል ኖሮ እኚህ የሃይማኖት አባት ይህንን ባልፈፀሙም ነበር ሌላም ለመጥቀስ ቢያስፈልግ በዘመኑ የታመሙ ድውያን በመንፈሳዊ ጸሎት የመፈወስ ችሎታ ያላቸው አባ ወልደ ተንሣኤ [illegible]ዛውን ለመጥቀስ እወዳለሁ እሳቸውም ለነፃነት ሀገር የለም ብለው በጣሊያን የእምነት አመት ወረራ ጊዜ ከኢትዮ[illegible] አርበኞች ጋር በአርበኝነት እንደሠሩ ከራሳቸው እንደበት የሰማሁ በመሆኔ ሳልገልጽ አላልፍም ሌላውን ለታሪክ አዋቂዎች እተዋለሁ ። ያም ሆነ ይህ ቀደም ያሉ አባቶቻችን ሃይማኖት አትግደሉ ይለናል ብለው ጠላትን ከመከራከርና አሳፍሮ ከመመለስ ገሸሽ ያሉበት ጊዜና ሰዓት ፈጽሞ አይገኝም ።

የሃይማኖታችን መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ ከኃይልና

ወይ. ገብ ፲፫ ዮሬል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# "ራሱን ያለ ምስክር አልተወም"

ሥራዎች ሁሉ የሠሪዎቻቸውን ማንነት ይመሰክራሉ ሕንጻ የሐናጺውን መጽሐፍ የጸሐፊውን ዕውቀትና ጥበብ ይገልጣሉ ፡፡ አምሮና ሠምሮ የሚታይ ሥራ ሁሉ ሠራተኛውን ያስመሰግናል የሠራተኛውን ችሎታ ይመሰክራል ፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ራሱን ለሰዎች ለመግለጥ ራሱን ያለ ምስክር የተወበት ጊዜ የለም ወደ ፊትም አይኖርም የእጁ ሥራዎች የሆኑት ሰማይና ምድር ሀልውናን ይመሰክራሉ በሰማይና በምድር ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ለእግዚአብሔር ሀልውና ምስክሮች ናቸው ፡፡ ሐናጺ ከሌለ ሕንጻ ጸሐፊ ከሌለ መጽሐፍ እንደማይገኝ ሁሉ ፈጣሪ ባይኖር ፍጥረታት ሊገኙ እንደማይችሉ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ያምናሉ ፡፡ የፍጥረተ ዓለምን አመጣጥና የእያንዳንዳን ሥነ ፍጥረት እንቅስቃሴ የሚያጠኑ ሊቃውንትም ሥራ ያለ ሠሪ እንደማይገኝና ሠራተኛም በሥራው እንደሚታወቅ አረጋግጠዋል ፡፡

ቅዱስ መጽሐፍም "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል ፡፡ የማይታይና የማይመረመር እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ይታወቃል" ፡፡ በማለት ይናገራል ፡፡ መዝ. 18 ፡ 1 ፡፡ ሮሜ ፩ ፡፳ ፡፡

እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የገለጠ በሥነ ፍጥረት ብቻ አይደለም በአንድ ልጁ በእግዚአብሔር ወልድ አማካይነትም ራሱን ለዓለም ገልጦአል እግዚአብሔር ወልድ ያለ ዘርአ ብእሲ በኅቱም ድንግልና ተወለደ ፡፡ በድንግልና የተወለደው በእደ ዮሐንስ በዮርዳኖስ የተመቀው ፤ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ ተሰቅሎ ለሰዎች ቤዛ የሞተውና በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው ከተነሣም በኋላ በአርባኛው ቀን ሰዎችና መላእክት እያዩት በምስጋና የዓረገው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ ያስረዳሉ ፡፡ ከዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ፡-

፩ኛ ሀ/ በኅቱም ድንግል መወለድ

ለ/ የእንስሳት እስትንፋሳቸውን መገበር

ሐ/ የሰብአ ሰገል ስግደትና እጅ መንሻ

መ/ መላእክት "በሰማያት ለእግዚአብሔር ምስጋና በምድርም ለሰው ልጅ ሰላም ሆነ" በማለት ሰላምን መስበካቸው

ሠ/ ኖሎት (እረኞች) ከመላእክት ጋር በአንድነት ማመስገናቸው እውነተኞች ምስክሮች ናቸው ፡፡

፪ኛ ተወለደ በ፴ ዓመቱ በአካለ ሥጋ ወደ ዮርዳኖስ ሂዶ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ

ሀ/ የዮርዳኖስ ውሃ ወደኋላ መመለስ መዝ ፻፲፫ ፡፫

ለ/ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ መቀመጡና አብ በደመና ሁኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ማለቱ የእግዚአብሔርን የአካል ሦስትነት የባሕርይና የሀልውና አንድነት አስረድቶአል ፡፡

ሐ/ እግዚአብሔር ወልድን ያጠመቀና በእጁ ራሱን የዳሰሰ "የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚለውን የአብን ቃል በጆሮው የሰማ ፤ የመንፈስ ቅዱስን በአምሳለ ርግብ መውረድ በዓይኑ ያየ ዮሐንስ አማናውያን ምስክሮች ሲሆኑ የዮሐንስ ምስክርነት እንዲህ የሚልነው "... መንፈስ እንደ ርግብ ሁኖ ሲወርድ አየሁ በእርሱ ለይም ኖረ እኔም አላውቀውም ነበር ፡፡ ዳሩ ግን በውሃ አጠምቅ ዘንድየላከኝ እርሱ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ ፡፡ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ ዮሐ ፩ ፡ ፴፪-፴፬ ፡፡

፫ኛ በገሊላ አውራጃ በቃና የሠርግ ቤት የተፈጸመው ተአምር፡ክርስቶስ የባሕርይ አምላክና ሁሉን ቻይ መሆኑን ሲያስረዳ በተአምር የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ የጠጡ ሁሉ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምስክሮች ናቸው ፡፡ ተአምራቱን አይተው ክብሩን ተረድተው አምነዋልና ፡፡ዮሐ፪ ፡፩-፲፩

፬ኛ በምድረ በዳ የተደረገው በረከተ ኅብስት አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ አበርክቶ ከአምስት ሺህ በላይ ሰዎችን መመገብ ከዚያም አሥራ ሁለት መሶብ ትርፍራፊ ማንሳት ራሱ ምስክር ሲሆን ከአምስት ሺህ በላይ የሆኑ ተመጋቢዎችና አምስት እንጀራ ከሁለት ዓሣ ጋር አቅርበው አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ ያነሡት ደቀ መዛሙርት ምስክሮች ናቸው ፡፡ ምስክርነታቸውም ዕውነት ነው ፡፡ ተመግበውና አይተው ተረድተዋል ፡፡

፭ኛ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ የታዩት ሰባት ተአምራት፡እነርሱም ሀ የፀሐይ መጥቆር ለ/ የጨረቃ ደም መሆን ሐ/ የከዋክብት መርገፍ መ/ የቤተ መቅደስ መጋረጃ መቀደድ ሠ የድንጋዮች መፈረካከስ ረ የመቃብራት መከፈትሰ የሙታን መነሳት ናቸውእነዚህ ሰባት ተአምራት በታዩ ጊዜ በመስቀልላይየነበረው ክርስቶስ አምላክ መሆኑንና ለሰዎች ቤዛ ሆኖ መስቀሉን ብዙዎች አምነዋል ፡፡ ወደእርሱም ተመልሰዋል ፡፡ ከብዙዎቹም አንዱ "ጌታ ሆይ በጌትነትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" በማለት አዳኝነቱንና ዳግመኛም ለፍርድ የሚመጣ መሆኑን አምኖ ምሕረትን የጠየቀው በቀኝ በኩል ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ ነው የክርስቶስን አዳኝነት ስለ አመነና ስለ መሰከረ በደሉንም ስለተናዘዘና "በመንግሥትህ አስበኝ" ብሎ ይቅርታን ስለለመነ ዛሬ በገነት በደስታ ከእኔ ጋር ትኖራለህ" የሚል የደኅንነት ቃልን ተቀብሎ በልዑል ፊት በደስታ ይኖራል ሉቃ ፳፫ ፡፵፪ ፡፡

6ኛ/ ትንሣኤውና ትንሣኤውን ያዩት

ሀ/ ክርስቶስ በአይሁድ ከመያዙና ከመሞቱ አስቀድሞ ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት እንደሚሞትና በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ይናገር ነበር አይሁድ ይህን ፈርተው ስልሳ ያህል በሚሆኑ ወታደሮች መቃብሩን አስጠብቀው ነበር ክርስቶስ በተነሣ ጊዜ እነዚህ ሁሉ አይተዋል መስክረዋልም ፡፡

ለ/ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበረበት መቃብር ባዶውን መገኘቱ

ሐ/ ወደ መቃብር ለሄዱት ሴቶች ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጉታላችሁ ተነሥቶአል በዚህ የለም" በማለት የመሰከሩ መላእክት ፡፡

መ/ የተከፈነበት የመግነዝ ጨርቅ ከመቃብር ውጭ ተጠቅልሎ መገኘቱ ዮሐ. ፳፡፭

ሠ/ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ለተለያዩ ሰዎች መታየቱ ለትንሣኤው ምስክሮች ሲሆኑ በራሱ ሥልጣን የተነሣው ትንሣኤ የአምላክነቱ ማረጋገጫ ምስክር ነው ፡፡

7ኛ ዕርገቱና በዕርገቱ ጊዜ የነበሩ፡ክርስቶስ የዓረገ ደቀ መዛሙርቱና መላእክት ሁሉ እያዩት ነው መላእክትም "የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል" በማለት እንደ እየሥራው ዋጋ ለመከፈል ዳግም የሚመጣ መሆኑን መስክረዋል ፡፡

"ክርስቶስ መከራን ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ ተጽፎአል ለዚህም እናንተም ምስክሮች ናችሁ" ተብለው ለምስክርነት የተጠሩ ሐዋርያት እያዩት ወደ ሰማይ ዓረገ እነርሱም ሰገዱለትና በደስታ ወደኢየሩሳሌም ተመለሱ ፡፡ ሉቃ ፳፬ ፡፵፮-፶፫ ፡፡

ከዚያም በኋላ ".... ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን ..... ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሠራ ከሰማይ ዝናምን ፡ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለምስክር አልተወም ፡፡" እያሉ ሲመሰክሩና ሲያስተምሩ ኑረዋል ፡፡ ምስክርነታቸውም ዕውነት ነው ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ሰዎችና መላእክት እያዩት
## በምስጋና ዐረገ



መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሳ በአርባ ቀን ሰዎች እያዩት በመላእክት ምስጋና አረገ ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በተለያዩ ሁኔታዎችና በሌሎች ኃይል ብዙ ሰዎች ዐርገዋል ። ለምሳሌ ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ በእሳት ሠረገላና በእሳት ፈረሶች እየተረዳ አርጉአል ። ፪ኛ ነገ. ፪ ፡ ፲፩ ።

ነቢዩ ኤልያስ ያረገው ፍጡር እንደ መሆኑ ከተፈጠረበት መሬት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እንዲሁም ሞትን ከመቅመሱ በፊት ከሞት ፊት ተሠውሮ ነው ።

ነቢዩ ኤልያስ በዚያ መንገድ እንደ ክርስቶስ እንዲህ ሊያርግ አልቻለም ። የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ስለ ኤልያስና ክርስቶስ ዕርገት ልዩነት እንዲህ ሲል በሃይማኖተ አበው ድርሳኑ ጽፎአል ። "ነቢዩ ኤልያስ በዚያ መንገድ እንደ ክርስቶስ እንዲህ ሊያርግ አልቻለም ። የኤልያስ ባህርይ በዚህ መንገድ ሊያርግ አልቻለም ። መላእክት ወደታዘዙበት ቦታ ወሰዱት እንጂ ። አንድ አካል አንድ ባህርይ፣ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ግን መላእክትን የፈጠረ ነውና በሥልጣኑ ዐረገ" ሃይማኖተ አበው ምዕራፍ ፷፯ ክፍል ፲፫ ቁ፲፪ - ፲፭" የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት የተለየ ክብርና ጌትነት የተመላበት የድል አድራጊነት ምልክት ስለሆነ ከፍጡራን ዕርገት የተለየ ነው ። ፍጡራን ቢያርጉም በመላእክት እርዳታና መሪነት ወደማያውቁት አገር ሲሆን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የፍጡራን ፈጣሪ አምላክ በመሆኑ በፈቃዱ ወደቀደመ ሉአላዊ መንበሩ ዐርጉአል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና የኖረ ፣ ወደፊትም ዓለሙን አሳልፎ በክብርና በጌትነት በመላእክት ምስጋና ለዘለዓለም የሚኖር ሲሆን ዓለምን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፣ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ፣ በመስቀል ላይ ሞቶ ፣ ሞትን ድል አድርጐ የዓለምን ደኅንነት ከፈጸመ በኋላ ነው ያረገው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበደል የወደቁትን የሰው ልጆች ነፃ ለማውጣት በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ብዙ መከራና ስቃይ ደርሶበታል ። ዓለም መድኃኒቱን አያውቅምና "መድኃኒታቸውን ጠሉ" ተብሎ እንደተጸፈው መድኃኒታቸውን በመጥላት አይሁድ መከራና ሥቃይ አደረሱበት ። ስለተቀበለው መከራ የእሲሱ ኢጲስ ቆጶስ ቅዱስ ጐርጐርዮስ በሃይማኖተ አበው ክፍል ፴፮ ከቁጥር ፳፯ - ፳፱ ፡ እንዲህ ብሏል ። "በፈቃዱ መከራን በሥጋው የተቀበለ መከራንም ሁሉ የታገሠ ፡ እርሱ ነው ። እንደበግ ሊሠዋ መጣ ፡ በግ በሚሸልተው ፊት እንደማይናገር አልተናገረም። በነገሩም ሀሰት አልተገኘበትም ። ነፍሱን ከሥጋው እስከመለየት ደርሶ በሁሉ መከራን ታገሠ።ሞቱም በመስቀል የተደረገ ነው ። በአንደበቱ አንድ ነገርን ስንኳ አልተናገረም ።" መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሶስተኛው ቀን በግርማ መለኮት በኃይልና በሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በ፵ኛው ቀን በድል አድራጊነት ምርኮውን ይዞ ወደነበረበት የክብር ቦታ መላእክትና ሰዎች እያዩት ዐረገ ። ምርኮ የሚለው ቃል ምን እንደሆነ ቅዱስ ጐርጐርዮስ ዘኑሲስ በዚሁ በሃይማኖተ አበው ምዕራፍ ፴፮ ከቁጥር ፴ - ፴፯ ፣ ምዕራፍ ፵፬ ቁጥር ፳ ፣ ላይ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል ።

"ከመስቀሉ ወደሲኦል በመውረዱ አዳነን ፣ በአባታቸው በአዳም በደል በሲኦል ተግዘው የነበሩ ጻድቃንን ፈታ። ከሙታን ተለይቶ አስቀድሞ በተነሣ በእውነተኛውም ትንሣኤው አስነሣን ። የገነትንም በር ከፈተልን ።" ከዚህ ሁሉ ድል አድራጊነት በኋላ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችና መልእክት እያዩት በክብር ወደ ሰማይ ያረገው የሐ. ሥ.፩ ፡ ፱ ፣

"ደቀ መዛሙርቱ ቅድስት ፣ ንጽሕት ትንሣኤውን ፣ በችንካር የተቸነከረ የእጁን ፣ የዕግሩን ምልክት (እትራት) ካዩ በኋላ በጦር የተወጋ የጐኑንም ምልክት (እትራት) ከዳሰሱ በኋላ ከትንሣኤውም በኋላ ወደሰማይ ዐረገ ። በአርባ ቀን ደቀ መዛሙርቱ እያዩት በተነሣበት ሥጋ ወደሰማይ ዐረገ ። ዳግመኛም ለጻድቃን ሊፈርድላቸው በኃጥአን ሊፈርድባቸው በዐረገበት ሥጋ ይመጣል ። ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋም ወደሰማይ ዐረገ ። በአባቱ ዕሪና ተቀመጠ ። የቀና ሃይማኖት ይህ ነው ። እንዲህ ብሎ የማያምን ሰው ቢኖር ሐዋርያት የሰበሰቡዋት ቤተ ክርስቲያን ትለየዋለች ። አምላክ ሲሆን በሥጋ ተገለጠ አንዱም ተለይቶ እንዳይቀር ሰው ሲሆን ወደ ሰማይ ዐረገ ይላል (ሃይማኖተ አበው ም. ፴፮፣፴- ፴፯ ም. ፵፯ ቁ ፴፫ በአጠቃላይ የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት ከሁሉም የተለየ በመሆኑ ያረገው ለዓለም አፅናኝ የዓለምንም ኃጢአት አስወጋጅ የሆነውን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለዓለም ሊልክ እና ወደቀደመ ክብሩም ከድል በኋላ ለመመለስ ጭምር ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያርግበት ጊዜ ተከታዮቹ የሆኑት ሐዋርያት ሁለት ዓይነት ነገር ደርሶባቸዋል ።

1ኛው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተለያቸው ማዘናቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ አፅናናቸውና ስለባረካቸው በዓይናቸው እያዩትም በመላእክት ምስጋና በክብር ስለአረገ መደሰታቸው ነው ።

የሐዋርያትን ሐዘን ለመግለጽ ወንጌላዊው ዮሐንስ "አሁን ወደላከኝ እሄዳለሁ ከእናንተም ወዴት ትሄዳለህ ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም ። ነገር ግን ይህን ስለነገርኋችሁ ኀዘን በልባችሁ ሞልቶአል ። ይላል" የሐ. ፲፮ ፡ ፮ ፣

በእርግጥ እንኳንስ ተአምራት የሚያደርግ ፣ ከሞት የሚያነሳ ፣ ድውዮችን የሚፈውስ፣ሲርብበተአምራት፣ብስትን አበርክቶ የሚያጠግብ ቅዱስ አምላክ ቀርቶ ሌላም የሚወዱት አቻ ጓደኛ ለሶስት ዓመታት አብሮ ከኖረ በኋላ ሲለይ እጅግ ያሳዝናል ። በዚህም ምክንያት ሐዋርያት አዝነዋል ። ለጊዜውም ተክዘዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ ጊዜ ሐዋርያት ተደስተዋል ። ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ይህንኑ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል" እስከቢታንያም አወጣቸው ፣ እጆቹንም አንስቶ ባረካቸው ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ። ወደሰማይም ዐረገ ። እነርሱም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ ። ሉቃስ ፳፬ ፣ ፶-፶፫ ፣ ሐዋርያት የተደሰቱት ለጊዜው ስለባረካቸውበረከቱንም ለእነርሱ ስለሰጣቸው ብቻ አይደለም ። ከእርሱ ባገኙት በረከት እነርሱም በመባረክ በሌላው ላይ በረከት እንዲያሳድሩ ስለፈቀደላቸው

ሲሆን፣እንዲሁም ሞተ ተነሣ፣ዓለሙንም በቅዱስ ደሙ አነፃ ፣ እያሉ የሚመሰክሩለት ቅዱስ አምላክ ሰዎችና መላእክት እያዩት በግልጥና በታላቅ ምስጋና ስለአረገና የሚያስተምሩትና የሚመሰክሩት በግልጥ ስለተረጋገጠ ነው ።

ከዚህም ሌላ የእነርሱ ደስታ የዓለም ደኅንነት ሙሉ ሆና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተፈጸመ ሐዋርያት እግዚአብሔርን ዘወትር እያመሰገኑ በቤተ መቅደስ ኖረዋል ። በምሥጢረ ድኅነት(ደኅንነት) ስንመለከተው በልደቱና በትንሣኤው የተጀመረው የዓለም ደስታ በዕርገቱ ፍጹም እንደሆነ እናያለን ፤ ስለእኛ ሰው ሆና የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ ባይሞት ሞቶም ባይነሣ ተነስቶም ባያርግ ኖሮ ደኅንነታችን ፍጹም ባልሆነም ነበር ።

ብዙ ሰዎች ስለሰው ልጅ መብትና ሕይወት ሲሉ መስዋዕት ሆነዋል ። ሆኖም ሞተዋና ተረስተው ቀርተዋል ። በእውነት ለሰው ልጆች ደኅንነት መስዋዕት በመሆን ሕይወቱን የከፈለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ተነሣ ። በተነሣ በአርባኛው ቀንም ዐረገ ። ለዘለዓለምም በድል አድራጊነት ይኖራል ። ዳግመኛም የሰውን ልጅ እንደሥራው ዋጋውን ይከፍል ዘንድ በክብር ይመጣል።

የጌታችን መድኃኒታችን ዕርገት በሐዲስ ኪዳን በሰፊው ተብራርቶ ይገኛል ። ከሁሉም ይልቅ በታሪክ ጸሐፊነት የታወቀው ቅዱስ ሉቃስ ፣ ቀኑን ቦታውንና ድርጊቱን በጥሩ ሁኔታ መዝግቦአል ። ለምሳሌ ፣ ስለቀኑ በተነሣ በአርባኛው ቀን ፣ ስለቦታው በቢታንያ ፣ ስለድርጊቱም መላእክትና ደቀመዛሙርቱ እያዩት በደስታ በታላቅ ክብር በመላእክት ዝማሬ እንደዐረገ ጽፎአል ። ሉቃ. ፳፬ ፣ ፶-፶፩ የሐ.ሥ. ፩ ፣ ፩-፲፩)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይል አድራጊነት ከሞት ከተነሣ በኋላ ለምን ዐረገ ደቀ መዛሙርቱንስ ለምን ተለያቸው ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በክብር የሚያርግ መሆኑ ተደጋግሞ በትንቢት ተነግሮ ነበር ። ዕርገቱም በድል አድራጊነት ፣ ምርኮውን ይዞ እንደሚያርግ ነቢያት በትንቢት አስቀድመው ተናግረውት ነበርና ይህ እንዲፈጸም ጭምር ነው ።

ለምሳሌ፣ነቢዩዳዊትእንዲህብሎአል ። "ወደላይ ዐረግህ ፣ ምርኮን ማረክህ ፣ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ" መዝሙር ፷፯ ፣ ፲፯ ።

አምላክ ፣ በእልልታ ፣ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ ። ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ ። መዝሙር ፵፮ ቁ.፭ ፣ በሌላ በኩልም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የሰማይና የምድር ጌታ በሁሉም ምሉዕ የሆነ ዘለዓለማዊ አምላክ

ወደ ገፅ ፲፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ርክበ ካህናት

ርክበ ካህናት ማለት መገናኛ ስብሰባ ጉባኤ ማለት ሲሆን እንዲህ ያለውም ጉባኤ ካህናትን የሚያቅፍ ስለሆነ እነሱን ያመለክታል ፤ በዚህ አኳኋን ካህናት ጉባኤ ሰርተውና ሰብስባ አድርገው የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዓትና ቀኖናን የሚደነግጉበት ለምዕመናን የሚሰጡትን ትምህርትና የሚያቀርቡትን አገልግሎት መክረው የሚያሻሽሉበት ስለ ችግራቸው ስለ ኅብረታቸውና ስለ ኑሮአቸው ተወያይተው ልዩ ልዩ መፍትሄ የሚሰጡበት የመተዳደሪያ ሕግ ወስነው የሚያስተላልፉበት በመሆኑ ዓመታዊ ስብሰባ ተብሎ ይጠራል ።

ይሰበሰቡ የነበረው ከትንሣኤ በዓል በኋላ በሐያ አራተኛው ቀን ሲሆን እንደሌሎቹ በዓላት ተውሳክ ያለውና በዓመት አንድ ቀን ረቡዕን ሳይለቅ የሚከበር መንፈሳዊ በዓል ሆኖ ኖሮዋል ይህም እንግዳ ነገር ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መንፈሳዊ ሥርዓት በመሆኑ ለብዙ ችግሮች መፍትሄ አስገኝቶአል ።

ይሁን እንጂ ርክበ ካህናት የተባለው ዓመታዊ ስብሰባ መቼ እንደተጀመረና ከየት እንደመጣ ለማወቅ ከሁሉ አስቀድሞ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል ።እንዲህ ያለውንም ጥናት በምንቀጥልበት ጊዜ በዘመነ አበው የነበረውንና የመጀመሪያ ካህን እየተባለ የሚጠራውን የመልከ ጼዴቅን የሕይወት ታሪክ መመልከት ያሻል ፤ የሱንም ታሪክ ያነበብን እንደሆነ አብርሃም ጠላቶቹን ድል አድርጎ ሲመለስ መልከጼዴቅ ወጥቶ እንደተቀበለው እንጀራና የወይን ጠጅ ሰጥቶ እንዳስተናገደውና እንደባረከው እሱም የልዑል የእግዚአብሔር ካህን እንደነበር ታሪኩ ሲያብራራ በዘመኑ የካህናት ጉባኤ ወይም ርክበ ካህናት መኖሩን አይናገርም ። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፲፬ ከቁጥር ፲፯-፳

ሳሙኤልም የስለት ልጅ እንደመሆኑ መጠን በእግዚአብሔር ቤት እያገለገለ እንዳደገ የታወቀ ነው እሱም ለሊቀ ካህናትነት የተመረጠው በርክበ ካህናት ወይም በካህናት ጉባኤ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥሪ እንደሆነ ታላቁ መጽሐፍ ይነግረናል ። ሳሙኤልም መልካም እረኛና በጸሎቱ በትሩፋቱ የምዕመናን ሕይወት ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንደነበር የህይወት ታሪኩ ሲያብራራ እሱ በሚያስተዳድርበት ዘመን ግን ርክበ ካህናት ወይም የካህናት ጉባኤ መኖሩን የሚገልጽ መረጃ አልተገኘም ።

ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰውን ጉባኤ ሙሴ እንደጀመረው ፤ ምንም እንኳ ዕለቱና ዓመቱ ተለይቶ ባይታወቅም በዘመነ ኦሪት እንደተጀመረ ፤ የሌዋውያን ጉባኤና የመንፈሳዊ አስተዳደር ሥነ ሥርዓት እንደነበር አንዳንድ መረጃ ተገኝቶአል በኦሪት ዘጸአት ም.፰ ከቁጥር ፲፫-፲፬ እንደምናገኘው ሙሴ አማቱ ዮቶር መክረው ምክር ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘው ጥቃቅን የሆነውን ነገር እነሱ የሚፈጽሙ ነገሩን ጨምቀው ወደ እርሱ የሚያቀርቡ ፤ በፍርድም ሆነ በአስተዳደር የሚረዱት ሰባ ሰዎችን ከሕዝቡ መካከል መርጦ አንድ ጉባኤ አቋቋመ ይህም ጉባኤ የመጀመሪያና ሕዝባዊ ጉባኤ እንጂ ካህናት ያልተመረጡበትና የካህናት ጉባኤ እንዳይደለ ከቃሉ ልንረዳ እንችላለን ። በኦሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ ፲፩ ከቁጥር ፲፮-፲፯ የሚለው ግን የካህናት ጉባኤ እንደተጀመረ ያመለክታል ይህውም በሙሴ አቅራቢነት ከእስራኤል ሽማግሌዎች መካከል የሕዝቡን ሸክም የሚሸከሙ ፸ ሽማግሌዎች ወደ መገናኛው ድንኳን ቀርበው ከሙሴጋር በአንድነት ቆመው በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተሾሙ ቃሉ ያስረዳል

ይህንንም መሰረት በማድረግ ኒውስ ባይብል ወይም የመልካም ዜና መጽሐፍ ቅዱስ ገጽ ፫፻፳፮ ስለዚህ ሁኔታ ሲጽፍ «መንፈሳዊውንም ሆነ ሥጋዊውን የሕዝብ አስተዳደር ደንብ የሚወስኑበት «ሳንሔድሪን » ወይም «ሳንሔድሪም» የተሰኘ ዐቢይ ጉባኤ ወይም ምክር ቤት ነበር ። ይህም ጉባኤ የሚመራው በሊቀ ካህናቱ የበላይነት ነበር ። የአባላቱም ብዛት ፸፩ ሊቃናትን የሚይዝ ነበር» ሲል ጽሁፉን ይደመድማል ።

ይህንንም ድርጊት እውነት ሊያደርገው የሚችለው የኦሪት ሕግ እንደተሰራ የሌዊ ነገድ ተለይቶ በክህነት እንዲያገለግል ሲደረግ የክህነት አገልግሎትም ሆነ አስተዳደር ፤ በጉባኤ እየተወሰነ የሚተላለፈው ጉባኤ ሁሉ በአሮንና በልጆቹ ይካሄድ እንደነበር ለማንም ግልፅ ነው ።

በዚህ አንፃር የሌዋውያን አለባበሳቸውና አኗኗራቸው ፤ የአገልግሎቱ ሥነ ሥርዓትና የመስዋዕቱ አቀራረብ የአሥራቱም ሆነ የበኩራቱ አከፋፈል ሁሉ በጠቅላላው በዚያን ዘመን የነበረው የቤተ ክህነቱ የአመራር ምቋመ ህግ እየተወሰነ የሚተላለፈው ከላይ በተጠቀሰው ጉባኤ እንደነበር ከተግባሩ ለመረዳት ይቻላል ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፫፻፲ ዓመተ ዓለም የነበረው የአይሁድ ረቢ የሆነው ስምኦን ዘጌስት ዓለም በሦስት ነገር ትቆማለች ፩ኛ በህግ ፪ኛ/በሥራ ፫ኛ ርህራሄ በማድረግ ነው ካለ በኋላ በዚያን ዘመን ስለ ነበረው ስለ ካህናት ጉባኤ ወይም ርክበ ካህናት አስተያየቱን ሲሰጥ የሊቃነ ካህናት ብቻ ሳይሆን በጉባኤው ሌዋውያንም እንዲገኙበት ያስፈልጋል ህግም ሥነ ሥርዓትም በተግባር ላይ የሚውለው ትንሹም ትልቁም ተመካክሮ ሲስማማበት ነው » ብሏል ።

ረቢው እንዳለው ዓለም በትክክል ልትቆም የምትችለው በውሳኔ በሚተላለፍ ህግ ብቻ ሳይሆን እውነተኛ ፍትህና ርትዕ የሚሰጡ ትክክለኛ መንፈሳውያን ዳኞች ሰዓት ፤ አክብረው የሚያገለግሉና የሚቀድሱ እውነተኞች ካህናት በእውነት ስለእውነት የሚሰሩ ሠራተኞች ወንጌልን የሚያስተምሩና በአደባባይ ቆመው ስለ ክርስቶስ በእውነት የሚመሰክሩ ፤ ከራሳቸው ይልቅ ሌላውን የሚወዱና ርኅራሄ ያላቸው አባቶች ሲገኙ ዓለም በሁለት እግሯ ስለምትቆም ሰላምና ፍቅር በሕዝብ ዘንድ ሊበዙ ይችላሉ ። ነገር ግን አስፈጻሚ ከሌለ የካህናት ስብሰባም ሆነ በየጊዜው ህግ መውጣት ጠቃሚ እንዳይደለ ስምኦን የተናገረው በቂ መረጃ ሊሆን ይችላል ።

የዓለም መድኃኒት የሆነው ክርስቶስም እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ዘመን ከላይ በተጠቀሰው ዐቢይ ጉባኤ ወይም ርክበ ካህናት እየተመከረበት ይተላለፍ የነበረው ህግ አማኞች የማይችሉትን ከባድ ቀንበር እያሸከመ እንዲመረሩ ከማድረጉም ሌላ እያንዳንዱን ሌዋዊና ካህን ከድህነት አዘቅት ውስጥ ጥሎት ነበር ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሳቸውን ከህግ በላይ ያደረጉትን በምቾት ላይ የነበሩትን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን እንዲህ እያለ ያዘልፋቸው ነበር ።

«ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም» ካለ በኋላ ትምህርቱን በመቀጠል «እናንተ ግብዞች ጸፎችና ፈሪሳውያን ከአዘሙድና ከእንስላል ከከሙንም አሥራት ስለምታወጡ ፍርድንና ምህረትን ታማኝነትንም በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተው ወዮላችሁ ፡ ሌላውን ስትተው ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር» ብሏል ። የማቴዎስ ወንጌል ፳፫ ቁጥር ፬-፳፫ ።

ክርስቶስ እንዳስተማረው ህግ አስፈጻሚ ከሌለው በውሳኔ መተላለፉ ብቻ ጠቃሚ ሊሆን አይችልም በተጨማሪም ሕግ ሲባል ትንሹንም ትልቁንም በእኩልነት የሚመለከት ካልሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም ስለዚህ የጉባኤ መቋቋም የአማካሪዎች መሰየም ዋጋ ሊኖረው አይችልም ።

ይሁን እንጂ ይህ ጉባኤ ወይም ርክበ ካህናት በዚያን ዘመን በጣም የታወቀና ከሞት ፍርድ በስተቀር ሙሉ ሥልጣን የነበረው ጉባኤ በመሆኑ በባለ ሥልጣኖችም ተፈሪነት ነበረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንኳን በጭፍሮች ተይዞ በጲላጦስ አደባባይ ለፍርድ እንዲቀርብና ተሰቅሎ እንዲሞት የተከራከረ ይህ የካህናት ጉባኤ ነው ። እንግዲህ በዘመነ ኦሪት የነበረው ርክበ ካህናት ወይም የካህናት ጉባኤ መልኩ ይህንን ይመስል ነበር ።

በዘመነ ሐዲስ ርክበ ካህናት እንዴት ተጀመረ ? የሚለውን ደግሞ እንመረምራለን ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ኃጢአት ሞቶ ከተነሳ በኋላ እስከ ዕርገቱ ድረስ አንዳንድ ጊዜ ለብዙዎቹ አንዳንድ ጊዜ ለጥቂቶቹ ደቀ መዛሙርት የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዓት ፤ መጽሐፈ ኪዳንን ፤ ትምህርተ ኅቡአትን ሲያስተምራቸው ቆይቶአል ። ወንጌላዊው ሉቃስ ከሞቱ እስከ እርገቱ እንዳስተማረ ገልጦአል ። የሐ.ሥራ. ም . ፩፡፩-፬

ይህንን መመሪያ በማድረግ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ « ወመሐረ እስከ አመ ዓርገ እምኅቤነ ይኩነነ ሰማዓ ተንሥአቱ ዘይሄሉ ምስሌነ» ሲል ዘምሯል ትርጓሜውም የትንሣኤው ምስክርነት ለዘለዓለም ከእኛ ጋር ይኖር ዘንድ ከእኛ እስከ ዓረገበት ጊዜ ድረስ አስተማረ ማለት ነው ።

ይህንንም ተግባር የሚያረጋግጠው ወንጌላዊው ዮሐንስ በምዕራፍ ፳፩ ከቁጥር ፲፭-፲፯ የጻፈውን ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ባህር አጠገብ ለሦስተኛ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ በተገለጠበት ወቅት ምሳ ከበሉ በኋላ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጣቸው «ጴጥሮስ ትወደኛለህን ? ከወደድከኝ ግልገሎቼን ፡ ጠቦቶቼን በጎቼን ጠብቅ አለው ይህም አነጋገር ኃላፊነትን፤ አስተዳደርን ፤ ማስተማርን በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያንን የአመራር ውሳኔ የያዘ ከመሆኑም ሌላ ይህም ድርጊት የተፈጸመው አብዛኛዎቹ ደቀ መዛሙርቱ በተገኙበት ጉባኤ መሆኑን ሊያመለክተን ይችላል ደቀመዛሙርቱም ይህንን መነሻ በማድረግ ከትንሣኤ በኋላ በ፳፬ተኛው ቀን በየዓመቱ ረቡዕ ቀን ርክበ ካህናት ወይም የካህናት ስብሰባ እንዲደረግ ወሰኑ ።

ይህም ጉባኤ ማትያስን በይሁዳ እግር ለሐዋርያነት እንዲመረጥ አድርጓል ማህበሩንም እንዲያገለግሉ ሰባት ዲያቆናትን መርጦ ሾሞአል ከዚህ ጊዜ ጀምረው ካህናት ርክበ ካህናት በተባለው ጉባኤ የገዛ ችግራቸውን በራሳቸው እየፈቱ ስለ ቤተ ክርስቲያንም አመራር መፍትሄ እየሰጡ እስከ ፫፻፲፩ ዓ.ም ድረስ እየተሰበሰቡ ውሳኔ ያስተላልፉ እንደነበረ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፩፻፶፱-፩፻፶፬ መመልከት ያሻል ።

ከዚያ በኋላ ግን ስብሰባው በካህናት መሆኑ ቀርቶ በጳጳሳት ደረጃ ሆነ ዛሬም ቢሆን በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት የካህናትን ችግርና የቤተ ክርስቲያንን አመራር የሚወስኑ ከሕዝብ የተመረጡ ሽማግሌዎች ሲሆኑ በምስራቅና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን የካህናትን ችግርና የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር የሚወስኑ ጳጳሳት ብቻ ናቸው ። ርክበ ካህናት የሚለው ስም በተግባር የተተረጐመበት ዘመን አልፎአል ለሁሉም ጊዜ አለው ተብሏልና ።

አለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ

## እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

ከገጽ ፰ የዞረ

ኃይል የክርስትና እምነት በዓለም ተዘርግታለች ። ለዘለዓለም ትኖራለች በዚሁ ኃይል ቤተ ክርስቲያን ጸንታ ትኖራለች ።

የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ስለ መንፈስ ቅዱስ በሰፊው ያስተምራል መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ (ጰራቂሊጦስ) የእውነትም መንፈስ እንደሆነ [illegible] ። [illegible] መንፈስ ቅዱስ እውነትን ያስተምራል፤ ወደ እውነት ይመራል ። እውነት ምን እንደሆነ ይገልጣል ። ሕይወትን ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበሉና በመንፈስ ቅዱስ የተወለዱ ሁሉ እውነትን ያውቃሉ እውነተኛ ሥራን ይሠራሉ ።

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት ሥራን አልጀመሩም ። በዚህ መሠረት አዲስ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ

ወደ ገፅ ፲፮ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ ነው ። ስለሆነም በግንኙነትም መለኮታዊ ሥልጣን ሁሉ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ነው ። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ ዓለማት ነው ። ለፍጥረታት ሁሉ ሕይወትን ይሰጣል ።

ዓለማትና በውስጣቸው ያሉ ነገሮች ሁሉ በተፈጠሩ ጊዜ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዚያ ነበር (ዘፍ. ፩ ፡ ፪) ይህም ሕይወትን ለመስጠት ነበር ። የኢዮብ ወዳጅ ኤሊሁ ስለሰው ሕይወት አመጣጥ ሲናገር "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወትን ሰጠኝ" ይላል (ኢዮብ. ፴፫፣ ፬) ። በዚህ መሠረት ሕይወት ከየት መጣ ? የሚል ጥያቄ ቢኖር ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ ሕይወት ካለው እንደ መጣ ለመመለስ መሞከር ይቻል ይሆናል ። እንግዲያውስ ሕይወት ካለው ነገር ያልተገኘ በመጀመሪያ ሕያው ሆኖ የተገለጠ ምንድን ወይም ማን ነው ? አዎ ለሀላዌው ምክንያት የሌለው ሕያው ሆኖ የተገለጠ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው ። ተፈጥሮ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ሕይወትን ያገኛል ። መንፈስ ቅዱስ የሕይወት ምንጭ ነውና ።

በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የሚያምኑ ክርስቲያኖች ሁሉ በሚቀበሉት ሥርዐተ ሃይማኖት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደሚከተለው ተጽፎአል ። "ሕይወት ሰጭ በሆነው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እናምናለን" መንፈስ ቅዱስ ሕይወትን ለፍጥረት ሁሉ ከመስጠቱ ጋር ዕውቀትንና ማስተዋልን ጥበብንና ኃይልን ይሰጣል ። (ዘጸአ. ፴፩ ፡ ፪ - ፯)

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ እንደተነገረ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ በዐሥረኛው በተነሣ በአምስተኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ እንደ ዐውሎ ነፋስና እንደ እሳት ነበልባል ሆኖ ለሐዋርያት ወረደላቸው ።

ይኸውም ለአዲሲቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት ለአዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትን ለመስጠት ነው ። በኦሪት ዘፍጥረት መጀመሪያ ላይ እንደተገለጠ ይህ ዓለም እምኀበ አልቦኀበቦ(ካለመኖር ወደ መኖር) የመጣ ሕይወትንም



እመቤታችን ድንግል ማርያም ባለችበት መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት እንደወረደ

ያገኘ በመንፈስ ቅዱስ ነበር ። በመጽሐፈ ኢዮብም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለሰው ሁሉ ሕይወት ሰጭ እንደ ሆነ ታይቶአል ።

በዚህ አንፃር ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተጀመረች ከዚህ የተነሣ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት አምሳኛው ቀን "የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን" ሆነ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ መድኃኒታችን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ለሠራው ሥራ ሁሉ መደምደሚያ ሆነ (ተ፩፪) እንዲህ ይላል "ቃል ሥጋን ነሣ ይህም እኛ መንፈስ ቅዱስን እንድንቀበል ነው" ። አዎ የእግዚአብሔር ወልድ ሰው የመሆኑ ዋና ዓላማ በደሙ ታጥበን ከኃጢአት ከነጻን በኋላ ንጹሕ በሆነው ልባችን መንፈስ ቅዱስ እንዲያድር ነው ።

በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ተገልጦ አል ። መጽሐፍ ይላል "ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ እግዚአብሔር ዓለምን ወደደ" ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ፍቅር በዚህ አልተወሰነም ። "መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ" በማለት ባናገረው ትንቢት መሠረት መንፈስ ቅዱስንም በምልአት ሰጠን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መልካም ስጦታ ሲናገር እንዲህ ይላል ። "እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለላጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁ ሰማያዊ አባትማ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው? (ሉቃ ፲፩፣፲፫) አዎ ሰዎች ለልጆቻቸው መልካም ስጦታን መስጠት ያውቃሉ ። ግን ከሁሉ በላይ የሆነ ታላቁ ሰጭ እግዚአብሔር ነው ። ታላቅ ስጦታውም የዚህ ዓለም ሀብትና ንብረት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ነው ።

ቅዱስ ሄሬንዮስ (ኢሬንዮስ) ስለ ሰው ሁኔታ በተናገረበት አንቀጽ የሚከተለውን ጽፎአል ። " ሰው ማለት ሥጋና ነፍስ ያሉት ከመሆኑም በላይ መንፈስ ቅዱስም ያለበት ነው ። ሰው በውስጡ መንፈስ ቅዱስ ከሌበለበት ሰው አይደለም ። መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ከሌለ ሌላው መንፈስ ርኩስ ያድርበታል ። ከሰው በታች ያደርገዋል" እርግጥ ነው ፣ ሰው ያለ መንፈስ ቅዱስ ሙሉና ፍጹም አይደለም መንፈስ ቅዱስ ካላደረበት ሊያምን እንኳ አይችልም (፩ቆሮ. ፲፪ ፡ ፫) ያለ መንፈስ ቅዱስ አንዳችም ችሎታ የለውም ።

ሐዋርያት በበዓለ ሃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት ኃይል ጥበብና ማስተዋል ድፍረትም አልነበራቸውም ። መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ግን በሁሉ ነገር ሙሉ ችሎታ ተሰጣቸው ። ይህም ሁሉ እንደሚሆንላቸው መድኃኒታችን ክርስቶስ አስቀድሞ"ኃይልን ከላይ እስተልብሱ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ"በማለት ነገሮአቸው ነበር ። ኃይል የተባለም መንፈስ ቅዱስ ነው ። ይሁን እንጂ ዝርው ኃይል ሳይሆን አካላዊ ኃይል ነው ። እነሆ በመንፈስ ቅዱስ

ወደ ገፅ ፲ ዞሯል



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

1. ሥዕላዊ ድርሰት
2. ተራኪ ድርሰት (ወይም ዜናን አጉላማሽ)
3. ገላጭ ድርሰት ተብለው የሚጠሩ የድርሰት ዓይነቶች ብዙ ጊዜ የተለመዱ ሲሆን የሁሉም ማስረጃ በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ውስጥ ተሰባጥሮ ይገኛል ።

ከነዚህም መካከል የመጀመሪያው "ሥዕላዊ ድርሰት እንደገና ሀ/ ገላጭ ድርሰት ለ/ ሐሳብ ሰጭ ድርሰት ተብሎ በሁለት ክፍሎች ይነገራል ፣ የነዚህንም ማስረጃ እንደሚከተለው ባጭር ባጭሩ እናሳያለን ።

### ሀ/ ገላጭ ድርሰት

የአንድ ነገር ምንነት ወይም የሰውን ማንነት መልኩን ጠባዩን ዓይነቱን ቅርፁን ይዘቱን ልማዱን መኖሪያውን ወይም የአንድን ነገር አሠራሩንና ጠቅላላ አቋሙን ገልጦ የሚያስረዳ ሐሳብ መግለጫ (መክሥተ ሐሳብ) ነው ።

### ለ/ ሐሳብ ሰጭ ድርሰት

የአንድ ነገር መልኩ ፣ ዓይነቱ ፣ ቅርፁና አሠራሩ ፣ ከየት መጣውና ባሕርዩ ጥምር ተብራርቶ ከተገለጠ በኋላ ደራሲው የበኩሉን አስተያየት አክሎ ተጨባጭ የሆነ ፍሬ ነገር የሞላበት መልእክት የሚያስተላልፍበት ድርሰት ነው ።

### 2ኛ ተራኪ ወይም ዜናን አጉላማሽ ድርሰት

አንድ ነገር ወይም ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ሁኔታው የደረሰበትን ጊዜና ቦታ ድርጊቱ ያስከተለውን ጥቅምና ጉዳት በቅደም ተከተል ከመነሻው እስከ መድረሻው በትረካ ወይም በማጉላመስ መልክ አደራጅቶ ማቅረብ የሚቻልበት የድርሰት ዓይነት ነው ። ለዚህ ማስረጃ የሚከተለውን አጭር ድርሰት እንመልከት ።

1ኛ/ የመድፍን ፀሩ ምሥጢር

ከአወዳሾቹ አንዱ ጥራዝ ነጠቅ ምሁር
"ከጥይት የሚያድን ከአደጋ የሚሰውር
የተፈተነ እስማት ልዩ መድፍን ፀር
የራስ መጠበቂያ አለኝ ይሉ ነበር ።
ባላገሩም ሆነ ከተሜውም ሳይቀር
ይወራረድና ባለመጠራጠር
መቶ ብር በመምዘዝ በትድሚያ ያስይዛል
ከካርታ ጥይት ጋር ምንም ነገር ሳይጉድል
ጠመንጃ ተሰጥቶት "በል ተኩስ" ይባላል
እያነጣጠረ ግንባር ለመበተን
ወይም ጀርባቸውን ከኋላ ለማቡነን
ቢተኩስ ቢተኩስ ደብቴ አይመቱም
መሞትም ይቅርና ትንሽ እንኳ አይቆስሉም
መቶ ብር ሁልጊዜ ይቀልባልእንደሰም።
ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ያራዳ ወጣት
መቶ ብር ሊከፍል ተወራርዶ ድንገት
ጠመንጃ ተሰጥቶት ተቀብለ ጥይት ።
ታዲያ ያራዳ ልጅ አልተሞኘም ከቶ
የደብቴን ጥይቶች ከካርታው አውጥቶ
ያልተደገመበት ሌላ ካርታ ጥይት
ከኪሱ አውጥቶ ካርታውን በመሙላት
አጉርሶ አመቻቸ በተደነቀ ስልት ።
የተደገሰውን ሞት ሳያስታውሱ
ደብቴ እምርባቸው ካባ እንደለበሱ
በትልቅ ቋጥኝ ላይ ወጥተው ተኩፈሱ
እስማቱ አልሰመረም ምክንያቱን እንጃ
ቃታውን ሲስበው በአደገኛ ፍርጃ
ፍንገል ብለው ቀሩ እንደቦና ጥጃ
ታዲያ የሚገርመው አደገኛ ነገር
የመድፍን ፀሩ የምሥጢር አሠራር
በላቮራቶሪ ውስጥ ገብቶ ቢመረመር
ያ የደብቴ ጥይት ድምፁ የሚያሽብር
ለካስ ባዶ ኖርጥል የወረቀት ነበር
እርሳሱን አውጥተው ባሩድ ብቻ እንዲቀር
አድርገውት ኖርጥል በተለየ አሠራር ።
ጥንትስ መብረቅ እንጂ አደጋ የሚጥል
ነጎድጓድ ብልጭታው መች ሰው ገድሎ ያውቃል?
እርሳስ ሲኖር እንጂ ጥይት የሚመታው
ድምፁ ቢያስተጋባ ባሩድ ምን ዋጋ አለው?
የመድፍን ፀሩ ምሥጢራዊ ጥበብ
ይህ መሆኑ ታውቆ የደብቴ ሞት ሰበብ
ከንቱ ሆነው ቀሩ ደግቸው ደመከልብ።

፪ኛ/ የጠንቋይ ቱማታ

አንዲት መካን ቆንጆ ልጅ መውለድ ፈልጋ
ሔደች ወደጠንቋይ ልትጠይቅ በዋጋ
ጠንቋዩም ደስ ብሎት ባለማወላወል
"በሕግ ካገባሽው ከመጀመሪያ ባል
መውለድሽ አይቀርም አውለያው ታርቆሻል
ተቀበይ ወንድ ልጅ ጀባ ብለንሻል"
ብሎ መልስ ሲሰጥ ሴትዮዋ ገርሞአት
"አይመስለኝም ጌታው ምነው እያወቁት ?
የሕግ ባሌ እኮ ካለፈ ሕይወቱ
ከሞተ ቆይቷል ፣ ልክ አሥር ዓመቱ"
ብላ መልስ ብትሰጥ ጠንቋዩ ተቆጣ
ነገሩ እሳፍሮት የሚያደርገው ቢያጣ
"ዝም በይ ፍየል ምላስ ምን አስለፈለፈሽ?
ቢሞትም ባይሞትም ትወልጃለሽ አልኩሽ
ከተጠራጠርሽ ቀድሞ ለምን መጣሽ?
እያለ አጉራባት በሐፍረት ተውጦ
የጠንቋይ ቱማታ ምን ተጨብጦ !

መደምደሚያ

ባለፃር ቃልቻ አስማተኛ ጠንቋይ
ኧረ ለመሆኑ አሁንም አለወይ ?
በእድገ ጦርነት አገር ስትወረር
ምድር ቀውጢ ሆና ሕዝበ አዳም ሲሸበር
"አስማተኛ ጠንቋይ ባለመድፍን ፀር
ባለእንደርቢው እሳት የምትፈጥር
አደባባይ ወጥተህ ሙያህን አስመስክር!
ተባበር ተብሎ ተጠይቆ ነበር ።
ዳሩ ግን ያን ጊዜ ማንም መልስ አልሰጠም
እንደወጣ ሽታ ሆና ቀርቶአል ሁሉም
በማይጨውም ጊዜ ጥንቆላ አልጠቀመም
ስለዚህ ጠንቋዩም አስጠንቋዩም ያርምም።

ቄ/ መከብብ አጥናው



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የ .ሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ
አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አስቀድሜ የአብ ፀጋ ፣የወልድ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ፣ከሁላችን ጋር ይሁን እያልኩ የመንፈስ ሰላምታየን አቀርባለሁ ፣

፩. የክርስቶስ ሥጋ ውንና ደሙን የሚቀበሉት አፃናትና በሥጋ ወደሙ የጸኑ መበለቶች እና ሺማግሌዎች ሲሆኑ ልጃገረዶችም ዕድሜያቸው ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ከሆናቸው መቀበል ይችላሉ ?

፪ኛ አንዲት ልጃገረድ ዕድሜዋለአቅመ ሄዋን ከደረሰ በኋላ ትቀበላለችን ? በአንድ አካባቢ በዚሁ ምክንያት ውዝግብ የተፈጠረ ስለሆነ ካህናትም አናቀብልም ስለሚሉ የማትቀበልበት ምክንያት እንዲብራራልኝ ።

፫- በቤተ ክርስቲያናችን በሚፈጸመው ሥርዓተ ቁርባን ላይ ያልገባኝ ነገር አለ እርሱም አንድ ሰው ይታመምና ቤተ ክርስቲያን ሄዶ መቀበል ሲገባው ከቤት መጥታችሁ አቁርቡኝ /አቀብሉኝ /ይልና ይልካል ፣በዚህ ጊዜ ካህናትም ሥጋውን ደሙን ይዘው ይሄዳሉ ። ይህ ለምን ይሆናል ? ለምን ሕመምተኛው ሂዶ እንዲቀበል አይደረግም ?

፬- ድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንደልብ ሲዳረስ እኛ በአለንበት አካባቢ ግን አናገኝም ። ለዚህም መፍትሔ እንዲፈለግና ለዚሁም ጋዜጣው በየጊዜው እንዲደርሳቸው የሚፈልጉ ምዕመናን ስለአሉ ማህበርተኛ ለመሆን የሚያስፈልገው ሁሉ እንዲገለጽልኝእናየማህበሩ አባላት ለመሆን የሚፈልጉትን እንዳሰባስብ ይደረግልኝ ዘንድ በሙሉ ተስፋ እጠባበቃለሁ ፣

ዲያቆን ንጋቱ ኃይሌ
ከሲዳማ አውራጃ ት/ቤቶች ጽ/ቤት
ሲዳሞ የመ.ሣ.ቁ.፳፩
ስልክ ቁጥር ፳፰

ዲያቆን ንጋቱ ኃይሌ የላኩዋቸው ጥያቄዎች ደርሰውናል ስለጥያቄዎ እናመሰግናለን ።

1ኛ/ ጥያቄዎ የክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን መቀበል የሚገባቸው እነማን እንደሆኑ እንድንገልጽልዎ የሚያሳስብ ነው ።

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ደም መቀበል የሚገባቸው መላው የሰው ልጆች ሁሉ እንጂ ሕፃን ፣ ሽማግሌ ፣ ወንድ ፣ ሴት ፣ ካህን ምዕመን ተብለው ሊለዩ ክቶ አይገባም ምክንያቱም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ መስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ ለዓለም ቤዛ የሆነው ለሰው ልጆች ሁሉ እንጂ በዘርና በነገድ በዕድሜና በጾታ ለተለዩ ፍጡራን አይደለምና ።

ከዚህም በቀር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ሥጋውንና ደሙን መስጠቱን እና ከዚህ ቅዱስ ሥጋና ደም ያልበላ የዘለዓለም ሕይወት እንደማይኖረው ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጾታል ታዲያ ሰው ሀይወቱን እንዴት ይጠላል "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ።" ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋየ ነው ።

እውነት እላችኋለሁ የክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ።ሥጋዬን የሚበላ ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ። አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሙቱ አይደለም ።ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘለዓለም ይኖራል ።የሐ ፮፥፵፩-፶፱ »

ታዲያ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ቆርሶ ፣ ደሙን አፍስሶ የሰጠው ለዓለም ሁሉ እንጂ ሕፃን ፣ ሺማግሌ ፣ ወንድ ፣ ሴት በመባባል በሥጋውና ደሙ እንዲለያይ ስላልሆነ የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል የዕድሜ መነሻና ጣሪያ ሊያግድ አይችልም ።

ስለዚህ ጠያቂው እንዳሉት የክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል ያለባቸው ሕፃናት ፣ መበለቶችና ሺማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ወጣት ልጃገረዶች ፣ ጐልማሶች በማንኛውም ዕድሜ ክልል ያሉ ሁሉናቸው ።

በእርግጥ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመታት በላይ የሆናቸው ልጃገረዶች በኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግማሾቹ በራሳቸው ፍላጐት ፣ በአንዳንድ ቦታ ደግሞ በካህናት ሲከለከሉ ይታያል ።



ሁኔታው እውነትነት አለው ። ምክንያቱም ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል ማንኛውም ሰው ሳይዘጋጅና በአንድ ዓይነት ዓላማ ሳይወሰን ማለትም ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ የሚሆናትን ሕጋዊ የትዳር ጓደኛ ፈልጋ ማግባት ፣ ወንድም እንዲሁ በሕግ መወሰን ወይም በምንኩስና መወሰን አለባቸው ። ከዚያ በፊት ግን ንጹሕ ነኝ ሥጋውን ደሙን መቀበል ይገባኛል ብሎ የሚቀርብ ቢኖር መከልከል እንደሌለበት በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ተዘርዝሮ ተገልጾአል ።

ከዚያ በፊት ግን ንስሐ መግባት ፣ መጾም ፣ መጸለይ ፣ ራሱንም በንስሐ ማዘጋጀት እንዳለበት ካህኑ ማስተማርና መምከር አለበት ፣ ካስተማረው በኋላ እበቃለሁ ብሎ ከቆረበ እኔ በበደላችሁ መተላለፍ የለብኝም ብሎ የራሱን ኃላፊነት ማውረድ ፣ በንስሐ ሳይታጠብ መቁረብም የሚያስከትለውን ቅጣት መግለጥ እንጂ አትቁረቡ ብሎ መከልከል አይገባም ። ከቅዱሳት መጻሕፍትም ትዕዛዙን ዘርዝረው ማስረዳት አለባቸው ። ከነዚህም የሚከተለው ሳይጠቀስ መታለፍ የለበትም ቃሉም የሚከተለው ነው «ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ፣ ወይም የጌታን ፅዋዕ የጠጣ ፣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ ። ሳይገባው የሚበላውና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ። ይጠጣልምና ።

ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ ። አያሌዎችም አንቀላፍተዋል ። ራሳችንን ብንመረምር ባልተፈረደብን ነበር ። ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠፃለን ፩ኛ ቆሮ ፲፩፥፳፯-፴፪ ፪ኛ ቆሮ ፲፫፥፭ »

ይህ የቁርባን መመሪያ እየተነገረው ደፍሮ በኃጢአት እያለ የሚቀበል ቢኖር በበደሉ የሚተላለፍ ራሱ ነው ። ይህ ሳይነገረው ባለማወቅ ቢቀበልና መምከርና ማስተማር ያለበት ካህን ባያስተምር ግን በበደሉ የሚተላለፈው ያላስተማረው ካህን ነው ።

ስለዚህም ከሰው ልጆች ወገን ሁሉ ራሱን መርምሮ ሥጋውን ፣ ደሙን እቀበላለሁ ቢል ካህናት ሊከለክሉት አይገባም ። የሚከለክለው የራሱ በደል ነው ።

ካህናት መከልከል እንደማይገባቸውም በፍትሕ መንፈሳዊ ተገልጾአል ።

«ከካህናትም ወገን አንዱ ባያቀብል የተወበትን ምክንያት ይናገር ። ምክንያቱን ባይናገር ግን ከምዕመና ከቤተ ክርስቲያን ይለይ ። ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፫ ቁ.፯ »

ስለዚህ ጠያቂው እንዳሉት ከ፲፭ዓመት በላይ ያሉ ልጃገረዶችም ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ሥጋውን ደሙን ለመቀበል እንችላለን ፣ ተዘጋጅተናል ፣ ፈቲው የለብንም ብለው ከቀረቡና በግልጽ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል የሚከለክሉ ምክንያተ ኃጣውዕ ካልታየባቸው በቀር ካህናት ሊከለክሉዋቸው ስለማይገባ መቀበል ይችላሉ ፪ኛው ጥያቄዎም በዚሁ መልስ ይጠቃለላል ።

፫ኛ/ የታመመ ሰው ወደቤቱ ሂደው ሥጋውንና ደሙን እንዲያቀብሉት ቢጠይቅ ሊያቀብሉት እንደሚገባ በቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓት መጽሐፍ ተገልጾአል ። በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፫ ቁጥር ፭፻፳ እንዲያውም የተገለጸው በልዩ ልዩ ምክንያት ከምዕመናን ቢለይም ቢወገዝም ፣ ከቤተ ክርስቲያን እንዳይደርስ ቢደረግም ሥጋውንና ደሙን መቀበል እየፈለገ ወደቤተ ክርስቲያን ለመግባት የማይችል ቢሆን ካህናት ካለበት ሂደው እንዲያቀብሉት የሚያዝ መሆኑ ነው ።

ይህ ሰው በተለይ የታመመና ለሞት የሚደርስ ከሆነ እንዳይከለከል ታዝዞአል ።

በመሠረቱ ይህ ሰው ከቤተ ክርስቲያን የተለየው በኃጢአት ምክንያት ሲሆን የታመመ ሰው ወደ ሐኪም መሄድ እንደሚያስፈልገውና በሽተኛው ወደ ሐኪም ለመሄድ ባይችል ሐኪሙ ወደበሽተኛው እንደሚሄድ ሁሉ ካህናትም ታሞ ለመሞት ወደሚያጣጥር ሰው ቅዱስ ሥጋውንና ደሙን ይዘው ሂደው እንዲያቆርቡት ሲጠይቃቸው መሄድና ማቁረብ አለባቸው እንጂ መከልከል የለባቸውም ። ይህም የሚፈጸመው በመጀመሪያ ክርስቲያን ሁኖ ሲኖር ሳለ በመካከሉ ለታመመ ሰው እንጂ ክርስቲያን ሳይሆን ቆይቶ ለሞት ሲቃረብ እንዲያቆርቡት ቢጠይቅ ሊሆን አይገባም ። ወደታመመው ሰው መሄድና ማቁረብ ያስፈልጋል የምንልበትም ያለምክንያት አይደለም ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው የታመመውን ዓለም ለመፈወስ የተኮነነውን ሰው ከዳግም ሞት ለማዳን ሲሆን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰዎችን ለማዳን በፈለገ ጊዜ እርሱ ወደሰዎች መጣ እንጂ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲሄዱ አላደረገም ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንኑ ሲገልጽ «ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም ማቴ ፱፥፲፪ » ብሏል ። ይህንን ሃሳብ ስንመለከተው ማንኛውም አስታማሚ ወደታመሙ መሄድ እንጂ ታማሚዎች ወደ አስታማሚዎች መሄድ ብቻ እንደሌለባቸው ስለሆነ ካህናትም ለመቁረብ የሚቀርቡትን ጤነኞች ብቻ ሳይሆን በሽተኞችን ጭምር በመሆኑ በሽተኞችን ወደቤታቸው እየሄዱ ማቁረብ እንደሚገባቸው ቤተ ክርስቲያናችን ትፈቅዳለች ።

፫ኛ/ ስለ ድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ እና ስለ ትንሣኤ መጽሔት እንዴት እንደማይደርሳችሁ ላቀ 'ባችሁት ጥያቄ ጋዜጣውና መጽሔቱ ባሚከተለ ው ሁኔታ ሊደርሳችሁ ይችላል ።

1ኛ/ ለድምፀ ተዋ ... ጋዜ ...

2✶10= 2.40

ለፖስታ አገልግሎት

20×24=4.80

ድምር 7.20

2ኛ/ ለትንሣኤ መጽሔት

50×12=6.00

ለፖስታ አገልግሎት እ

20×12=2.40

ጠቅላላ ድምር ብር 15.60

በፖስታ ሐዋላ ማንኛውም ፈላጊ ቢልክልን መጽሔቱና ጋዜጣው በየጊዜው እንዲደርሰው እናደርጋለን



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ከፍተኛ ታሪክ ያለው ዮሐንስ አፈወርቅ በሶሪያ አንጾኪያ በምትባል አገር በ፫፻፵፱ ዓ.ም. ተወለደ። አባቱ የምሥራቅ ጦር አዛዥ ጄኔራል ሲሆን እናቱ ግን ከአሕዛብ ወገን ነበረች በሥራዋና በሕይወትዋ ሁሉ የምትመሰገን ደግ ሴት እንደነበረች ይነገርላታል።

ዮሐንስ እንደተወለደ አባቱ ስለሞተ ያደገውና የተማረው በእናቱ ብቻ እየተረዳ ነው። እናቱም ወደ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያዘነብል ትመክረው ነበር የሃያ ዓመት ወጣት ሳለ በአንጾኪያ ወደሚገኝ አንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብቶ በመማር ላይ እንዳለ ተጠመቀ። በ፳፩ ዓመት ዕድሜው መዓርገ ዲቁና ተቀብሎ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ጀምሯል። በ፴፩ ዓመት ዕድሜው ስለ ሥርዓተ ምንኩስናና መነኮሳት ፣ ስለ ሥልጣነ ክህነትና ስለካህናት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስረዳ ድርሰት ጻፈ። በዚህ ድርሰቱ ከዚያ በፊት ይፈጸም የነበረውን የመዓርገ ዲቁና አሰጣጥ ሥርዓት ተቃውሞአል ፣ ምክንያቱም የሰባት ዓመት ልጆች መዓርገ ዲቁና ይቀበሉና በዲቁና ያገለግሉ ስለነበረ የሰባት ዓመት ብላቴኖች ይህን መንፈሳዊ መዓርግ ለመቀበልና አገልግሎቱንም ለማከናወን እንደማይበቁ ገልጦአል። ቀሳውስትም ቢሆኑ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንንና ነገረ መለኮትን በሚገባ አውቀው ለሌላው የሚያስተምሩና የሚያሳውቁ ካልሆኑ መዓርገ ቅስናን መቀበል እንደማይገባቸው አስረድቶአል።

ከዚህም ሌላ በ፫፻፹፰ ዓ.ም. የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን እየተረጐመ ጽፎአል። ስለ በዓላት አከባበርና ስለ ሃይማኖት ስለ ፍቅርና ስለ ሕግ እንዲሁም ስለ ማኅበራዊ ኑሮና ግብረ ገብነት ጽፎአል አስተምሮአል ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ሲናገር “ሁሉን ለማድረግና ለመወሰን የሚችል ሁሉን የሚመለከት፣ለፍጥረታት ሁሉ መገኘት ምክንያት የሆነ በቃሉ ታላላቅ ተአምራትን የሚያደርግ አምላክ ነው። እነሆ በእርሱ ፈቃድ ፍጥረታት ሁሉ በቦታቦታቸውን ይዘው ይገኛሉ። ...” ከአለ በኋላ ስለ ሀልዎተ እግዚአብሔርም ሲናገር “የእግዚአብሔርን ሀልዎና ሁሉም ሰው ሊረዳው አይችልም ይሆናል ለተለዩ ሰዎች ሊገባቸው ባይችል ለሌሎቹ ግልጥ ሁኖ ይናረል ሰዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ሊያውቁ አይችሉም። ግን አስታዋዮች በመጠኑ ያውቃሉ፣ ከዚያም በመጠኑ ካወቁት ድንቅ ሥራው (ሥነ ፍጥረት) የተነሣ ሀልዎቱን ይረዳሉ” ይላል።

ስለ ጠባቂና ተጠባቂ ማለት ስለ ክርስቶስና ክርስቲያኖች ወይም ስለ መምህራንና ምእመናን ሲናገር “ምን እያለሁ? ጠባቂው የለም ነገር ግን በጎቹ በመልካም ሁኔታ ተሰብስበዋል። ይህን መልካም ውጤት ያስገኘው የእረኛው ትጋት ነው። በጎቹም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።ይኸውም እረኛው በሚኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን እረኛው ከእነርሱ በሚለይበት ጊዜ ሌላ ነጣቂና አስደንጋጭ እንዳይመጣባቸው ነው።” ይላል ይህ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች “ ወዳጆች ሆይ ሁልጊዜ እንደታዘዛችሁ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ” በማለት የጻፈላቸውን መልእክት ይመስላል። ፊል.፪ ፲፪።

ስለማኅበራዊ ኑሮም ሲናገር ችግሮችን ሁሉ ዘርዝሮ ከአስረዳ በኋላ በተለይ ለአብዛኛዎቹ ችግሮች መንሥኤ የሚሆነው አብዛኛውን ጊዜ ስካር እንደሆነ ይገልጥና“ ስካርንም የፈቃድ ዕብደት ነው።” ይለዋል።

ስለ ምሥጢረ ሥጋዌም ሲጽፍ “...ተዋሕዶንም እስረዳለሁ እግዚአብሔር ቃል በአካሉ ፍጹም የሚሆን ነፍስ፣ዕውቀት ያለው ሥጋን ከእኛ ባሕርይ ነሥቶ አልና፣ እርሱንም ተዋሕዶአልና። ስለ ዚህም ነፍስንና ሥጋን ተዋሕዶ ሰው የሆነ እግዚአብሔር ቃል አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደሆነ እንናገራለን ነገር ግን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ፩ እንደሆነ ብንናገር ወዲህም ከእኛ ባሕርይ የተገኘ ሥጋ ያለ መለየት በማይመረመር ተዋሕዶ ከቃል ጋር አንድ መሆኑን እኛ እናውቃለን። ሥጋ የመለኮትን ባሕርይ እንዳልለወጠ መለኮትም እንዲሁ የሥጋን ባሕርይ አልለወጠም። እርሱ ወልድ በተዋሕዶ ሰው የሆነ አምላክ ነው።

የቅዱስ ጳውሎስንም ትምህርት እየተረጐመ ሲያስተምር “እነሆ እርሱ ጳውሎስ አብን አምላኩ ለክርስቶስ አለው ፣ በውኑ ወልድ ክርስቶስ በክብር ከአባቱ ያንሳልን ?” በማለት ከጠየቀ በኋላ ሲመልስ“ከአብ አያንስም ደፍሮ ይህን የሚናገር ማንም ሰነፍ የለም መጽሐፍ ለአባቱ አንድ ልጅ እንደመሆኑ እንደ አባቱ ክብር ያለ ክብሩን አየነ ያለ አይደለምን?።ነገር ግን እርሱ በዚህ ክርስቶስ በውነት ሰው እንደሆነ አስረዳ። ዳግመኛም በተነሣ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መሆኑን አስረዳ ፈጽሞ ከእርሱ ወደ አልተለየው ወደ አብም ከመዓረጉ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አምላኬ አምላካችሁ አለ። ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላቸው ሰው የሆነ እርሱ እግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ አቡየ ብሎ ከዚህ በኋላ አምላኪየ አለ እንጂ” በማለት በዮሐንስ ወንጌል ፳ ፣ ፲፯ ያለውን ተርጉሞ ሲያስረዳ በሚከተለው ሁኔታ አብራርቶአል።” እኔ ሰው የሆንኩ አምላክ ነኝና እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጌአለሁና ኃጢአት የሌለበት እርሱ ነፍስንና ሥጋን በውነት ተዋሕጄ አለሁና ከእኔ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ላደረግሁት ለሥጋ ሥርዓት እንደሚገባ እንዲህ አባቴን አምላኪየ ብዬ ጠራሁት ይላል። (ሃይ.አበ.ም. ፷፯ ፣ ፲፱)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትንሣኤው ለደቀ መዛሙርቱ “ከእናንተ ጋር እስከምመጣበት ቀን ድረስ ከዚህ የወይን ጭማቂ አልጠጣም በሐዲስ ግብር በምንገባበት ጊዜ የምታዩኝ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ።” በማለት በማቴዎስ ወንጌል ፳፮ ፣ ፳፱ ያስተማረውን ሲተረጉም “ሐዲስ ያለው ይህ ነገር ምንድነው? ይህ ነገር ድንቅ ነው።መዋቲ ሥጋ እንዳለኝ ታያላችሁ ነገር ግን ከትንሣኤ በኋላ ቢበላና ቢጠጣ መብልን ሽቶ አይደለም ፣ እርሱ ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሣ ያምኑ ዘንድ በላ ጠጣ እንጂ ይህ ድንቅ ሥራ ነው ያለመለወጥ ሰው የሆነ ቃል የተቸነከረበትን ምልክት (እትራት) አላጠፋምና በሚሞቱ ሰዎች እጅ እንዲዳሰስ አድርጎታልና አምላክ የሆነ ሥጋ የሚታይበት ጊዜ ነውና አላስፈራም እርሱ በዝግ ደጅ ገባ ነገር ግን በትንሣኤው ያምኑ ዘንድ የተሰቀለው እርሱ እንደሆነ የተነሣውም ሌላ እንዳይደለ ያውቁ ዘንድ ይህን ሠራ።...ከትንሣኤ አስቀድሞ ደቀ መዛሙርቱ ጥዋትና ማታ ከእርሱ ጋር ይበሉ እንደነበረ ከትንሣኤም በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በላ። ስለዚህም ከትንሣኤው በኋላ ያየነው ከእርሱም ጋር አብረን የበላን የጠጣን እርሱ ነው ብለው በአራቱ መዓዘነ ዓለም ትንሣኤውን አስረዱ” በማለት ጽፎ አስተምሮአል (ሃይ አበ ም. ፷፯ ክ.፷ እና ፷)

ይህ ታላቅ መምህር ከ፫፻፹፮-፫፻፺፰ ዓ.ም. እጅግ ታዋቂና ዝነኛ ሰባኪ ሆኖ ነበር። በዚህም ጊዜ ውስጥ በኦሪት ዘፍጥረት በማቴዎስና በዮሐንስ ወንጌል በሮሜ በቆሮንቶስ በገላትያ ፣ በኤፌሶን በጢሞቴዎስና በቲቶ መልእክታት እጅግ ተደናቂና ተደማጭ የሆነ ስብከት አዘጋጅቶ አስተምሮአል።

ከስብከቱ ለዛና ውበት የተነሣ ሊቀ ጳጳስ ፍላብያኖስ “አፈወርቅ” ብሎ ሰየመው ፣ “አፈወርቅ” የሚለውን የቅጽል ስም የሰየሙት ትምህርቱን አዘውትረው ያዳምጡ የነበሩና በጣዕመ ትምህርቱ የረኩ ምእመናን ናቸው የሚል ታሪክ አለ ፣ ያም ሆነ ይህ በትምህርት አቀራረቡና በንግግር ስልቱ “አፈወርቅ” እንደተባለ በታሪክ ተረጋግጦአል። ከትምህርቱ ተደማጭነት የተነሣ በዘመኑ የነበሩት ምእመናን “የዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት ከሚታጐል.. ብትጠፋ ይቀላል” ይሉ ነበር ይባላል።

በ፫፻፺፰ ዓ.ም. የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ በዘመኑ የነበረችው ንግሥት አውዶክስያ የአንዲት ድሃ ሴት ርስት እንደቀማች ሰማ፣“መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ” ፊት አይቶ የማያዳላ ደሃውን በድኅነቱ የማይንቅ ፣ ባለጸጋውንም ስለ ሀብቱ ብዛት ብቻ የማያከብር ሁሉን በእኩልነት የሚመክርና የሚገሥጽ ደግ መምህር ነበርና የድሃዋን ርስት መንጠቅ አግባብ አለመሆኑን ገልጦ ስለ ገሠጸት በደሴት እጥረክያ አስጋዘችው። የሮሙ ንጉሥ አናሬዎስና ሊቀ ጳጳሱ ዩናክንዲናስ ከንግሥቲቱ ባል ከአርቃድዮስ ጋር ተነጋግረው አስፈትተውት ነበር። ግን ንግሥቲቱ አውዶክስያ አልተስማማችም ነበርና እንደገና ወደ ስደት ቦታው እንዲመለስ አዘዘች። በዚህ ጊዜ የንግሥቲቱ ታዛዦች እያዳፉ ሲወስዱት ግንቦት ፲፪ ቀን ፬፻፯ ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በመንገድ ላይ አረፈ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የዚህ ታላቅ መምህር ትምህርት ለእምነትዋና ለትምህርትዋ ተስማሚ ስለሆነላት በአስረጅነት እየጠቀሰች ታስተምራለች ዕለተ ዕረፍቱንም ባመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት በየዓመቱ ግንቦት ፲፪ ቀን ታስታውሳለች።

ራድ አስረስ

---

# ደብዳቤዎች.....

ከገፅ ፩ የዞረ

ከጦርነት ይልቅ ሰላምና ፍቅርን መመሪያ አድርጎ መኖርን በሰፊው ያስተምረናል። ፍቅር ሃይማኖት ተስፋ በእምነት ታሪክ ውስጥ የማይለያዩ ቢሆኑም ከዚህ ውስጥ በላጩ ፍቅር እንደሆነ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ እናገኛለን። ስለ ፍቅር ካነሳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንድነትና ስለ ፍቅር እንዲህ ብሎአል እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ። (ዮሐ.ም. ፲፫ ከቁ. ፴፬-፴፭)።

ሐዋርያው ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው አንደኛው መልእክቱ ላይ ምዕራፍ ፲፫ በሚገባ ስለ ፍቅር አብራርቶአል ከጻፋቸውም ጥቂቱን ለመጥቀስ ቢያስፈልግ “በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኛለሁ ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ ተራሮችን እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ ይላል። ስለዚህ ከጦርነት ከግጭት ይልቅ ሰላም እንደሚመረጥ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል። ነገር ግን የሰላምንና የፍቅርን ትርጉም ለማያውቅየሰይጣንን ፈለግ ተከትሎ አንድነትንና ጸጥታን ለማደፍረስ በወራሪነት ለሚመጣ ጠላት ሃይማኖት ቆራጥ የሆነ ወኔ እንዲኖረን እንጂ እንድንልፈሰፈስ አያስተምረንም ሐዋርያው ጳውሎስ ከተናገረው እንጥቀስ እንደኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስ ከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም ደግሞ በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል የድሉን አክሊል አያገኝም (2ኛው ጢ.ም. 2 ከቁ.3 - 6/ ይላል።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጽላት ተቀርጾለት የሚገኘው በሰማዕትነቱ ወደር የማይገኝለት ቅዱስ ጊዮርጊስን መጥቀስ ለዚህ ዓላማ ጠቃሚ ይሆናል።





www.ethiopianorthodox.org

የቅ. ጊዮርጊስ ዜና ገድሉ እንደሚያስረዳን ቅ( ጊዮርጊስ እጅግ ኃይለኛና ለጠላቱ የማይበገር የጦር መኰንን እንደሆነ ይናገራል ። ቅ. ጊዮርጊስ ለአምስት ሺህ ሠራዊት አለቃ እንደሆነም ይገልጣል እንዲያውም ቅ. ጊዮርጊስ በጠላት መካከል ከነፈረሱ ሲገባ ጠላት የሚደርስበት እንደሚጠፋና ድልን ይጎናጸፍ እንደነበር ይገልጽልናል ቅ. ጊዮርጊስ በሃይማኖቱም በኩል ሊቀ ሰማዕት የተባለ እንደ እርሱ ያለ ተጋድሎ ከእሱ በፊትም ሆነ በኋላ ያደረገ ወይም የሚያደርግ እንደሌለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነገረው በገድሉ ተጽፎአል ። እንደዚሁም በቅዱስ ወንጌል በተለይ በሐዋርያት ሥራ ላይ ጻድቅነቱ የተመሰከረለት የሙፆ አሊቃ ቆርኔሌዎስ በሃይማኖቱ በኩል ጻድቅ ሆኖ ሳለ እምነቱ የወታደርነት ዓላማውን አላዘናጋውም (የሐዋ.ሥ.ምዕ.፲) በተጨማሪም በራዕየ ዮሐንስ ላይ የመጀመሪያ ውጊያ በሰማይ እንደተጀመረ ይገልጽልናል "በሰማይ ሠልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም ከዚያም ወዲያ በሰማይ ሥፍራ አልተገኘላቸውም ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ "ብሎ የዲያብሎስን መውደቅ ቢያስረዳንም እዚህ ላይ የሚሰጠን ሌላ ትምህርት ደግሞ እንደዲያብሎስ በዕብሪት ተውጦ ፈጣሪውን እንደተፈታተነና ውድቀት እንደደረሰበት ሁሉ በምድርም የሱን ፈለግ ተከትለው የአንድን ሀገር ሰላምና ጸጥታን ለማደፍረስ በዕብሪትና በግፍ ለመውረር የሚመጣን ጠላት የሊቀ መልአኩን የቅዱስ ሚካኤልን ፈለግ ተከትሎ የመጣን ዕብሪተኛ ጠላት አፀፋውን መልሶ ማዋረድ የሚያስፈልግ መሆኑን ያስተምራል ። በሌላም በኩል በአዋልድ መጻሕፍት እንደምንረዳው ቅዱስ ገብርኤል ለገላውዴዎስ ጠላቶቹን ይረታበት ዘንድ የእሳት ሰይፍ እንደሰጠው ያስረዳናል ። ከዚህም የበለጠ በሃይማኖታችን ይዘት በበለጠም ለመጥቀስና ለማስረጃነትም ለማቅረብ ይቻላል ።

በአጠቃላይ ሀብትን ፣ የሀገርን ነፃነትን በዕብሪት ለመቀማት የሞከረን ጠላት ከዓለው መጥፎ ሰይጣናዊ ዓላማ እንዲመለስ የሰላምን ፈለግ እንዲከተል መጠየቅ ነገር ግን ትዕግሥትን እንደ ፍርሃት ሰላምን ፍለጋ እንደ ሽንፈት ቆጥሮ አረመኔያዊ ተግባርን ለሚፈጽም የእግዚአብሔርን ኃይል ተገን አድርጎ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ ይነግረናል እንጂ ለእሳት እንደ ቀረበ ጭድ ሆነህ እጅህንና እግርህን አጣምረህ ጠብቀው ብሎ አላስተማረንም ።

ነገር ግን የመግደል አስከፊነቱ ሰውንም አትግደል ተብሎ በሃይማኖት ሕጋችን ውስጥ እንዳንፈጽመው የተከለከልነው በቅንዓት ተነስቶ በገንዘብ ተገዝቶ በስካር መንፈስ ተገፋፍቶ በማይረባ ነገር ሰውን መግደልንና የመሳሰለውን እንጂ ሕገ ወጥ አድራጊውን ስለአይደለ ከመናገር በፊት ማወቅ ይቅደም እያልኩ ጽሑፌን በዚሁ እደመድማለሁ ።

ወታደር በሻህ ገ. ወልድ
ፖሊስ ማሰልጠኛ ድሬድዋ
ፖ.ሣ.ቁ.300
ስ.ቁ. 113375

# ሰዎችና መላእክት እያዩት.....

ከ፳ኛ ገጽ የዞረ

ሲሆን ወደዚህ ዓለም የመጣው ግን ዓለምን በቅዱስ ደሙ ሊያድን ስለሆነ የመጣለትን የአዳኝነት ሥራ ፈጽሞ ከተነሣ በኋላ በዚህ ዓለም ሲዘዋወር አንድ ጊዜ በባህር ዳር ፣ በሌላም ጊዜ በዝግ ቤት እየታየ ቢኖር ምትሀት ወይም መንፈስ እየተባለ ሲጠረጠር ከመኖሩም በላይ እስከመስቀል ሞት ድረስ የሠራው ሥራ ሁሉ ከሌሎች ባልተለየም ነበር ።

ይህ ሁሉ እንዳይሆን መለኮት ፈቃዱ ስለሆነ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ፣ በጠቅላላ ሰላሳ ሶስት ዓመት ከአራት ወር ከ10 ቀን በዚህ ዓለም ኖሮ ወደሰማይ ዐረገ ። በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ። ከዚህም ጋር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባያርግ መንፈስ ቅዱስ ስለማይወርድ የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማረግ አስፈልጎአል ዮሐ. ፲፮ ፥፯ ከማረጉ በፊት ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ልዩ ልዩ ትምህርቶችን አስተምሮ ደቀ መዛሙርቱም ትምህርቱ በእነርሱ ዘንድና በዓለምም ሁሉ እንዲኖር ያደረገላቸው መሆኑን ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ብሎአል ።

"ዓቢይ ዜማ ተሰምአ በሰማይ ዘመላእክት ግናይ እንዘ የዐርግ ወልድ ዲበ መንበሩ ፣ ኩሎሙ መላእክት ትንሣኤሁ ዘመሩ" ታላቅ የመላእክት ምስጋናና ዜማ በሰማይ ተሰማ ፣ ወልድ ወደ ቀደመ ክብሩ ሲያርግም መላእክት ስለትንሣኤው አመሰገኑ ።"

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በለበሰው ሥጋ የዓለምን ነፍሳት አድኖ ማረጉንም ይኸው ቅዱስ ያሬድ ሲገልጽ "ጸርሐ ገብርኤል እምሰማይ ዘይብል መጽአ ወልደ እምላክ ለቢሶ ሥጋማርያም ፣ ወዔዋዎ ነፍሳተ ዓለም" ። ገብርኤል ከሰማይ ሆኖ እንዲህ ሲል ጮኾ ተናገረ ። ወልደ አምላክ ክርስቶስ የማርያምን ሥጋ ተዋህዶ ወደሰማይ መጣ ፣ የዓለም ነፍሳትንም ማረከ" ብሏል በሃይማኖታችን መሠረተ ትምህርት በጸሎተ ሃይማኖት "ወደሰማይ ባረገው በአብ ቀኝ በተቀመጠው በክርስቶስ እናምናለን" ተብሎ ከአስራ ሁለቱ የጸሎተ ሃይማኖት አንቀጾች አንደኛውን ክፍል ይዞ ይገኛል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣለትን አዳኝነት ፈጽሞ ሁሉን ነገር አስተካክሎ ወደቀደመ ክብሩ ዐርጐ ፍጥረታት ሁሉ ለዘለዓለም የሚገዙለት፡

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል



# የወጣቶች አምድ

አዘጋጅ፡- ኢሣይያስ ወንድም አገኘሁ

## የሥላሴ ትምህርት ቤት መዋለ ሕፃናት



የካቴድራሉ ዋና ጸሐፊ ከጋዜጠኛ ለቀረቡላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ

በመንበረ ፀባዖት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል ሥር የሚካሄደው የሥላሴ ትምህርት ቤት መዋለ ሕፃናት በ1974 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን የሥራ ይዞታውን በማሻሻል ከአለፈው የበለጠ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

በዚሁ መዋለ ሕፃናት ለጊዜው ከ፻፶ የማያንሱ ሕፃናት በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን አራት መምህራን ፣ሁለት ሞግዚቶች አንድ ምግብ አዘጋጅና አቅራቢ ፣ዘበኛ ጭምር በካቴድራሉ ተቀጥረው በማገልገል ላይ ናቸው ። መዋለ ሕፃናቱ ከምግብ ማደራጃውና ከዕቃ ቤቶቹ ሌላ ለጊዜው አራት የትምህርት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚሁ ፻፶ የሚሆኑት ሕፃናት በነዚሁ ክፍሎች ተመድበው ያለችግር በማመር ላይ ናቸው ይህንኑ ሁኔታ ለመመልከት በቦታው በተገኘንበት ወቅት ከዲያቆን ከፍያለ መራሂ የካቴድራሉ ዋና ጸሐፊ ጋር ያደረግነው ውይይት ስለመዋዕለ ሕፃናቱ ዕድገት የበለጠ ለመረዳት አስችሎናል ።

ከዋናው ጸሐፊ ባገኘነው ሪፖርትና ተዘዋውረንም እንዳየነው በ፲፱፻፷፬ዓ.ም.ሦስትሺብርወጭሆኖበግቢውውስጥ መሬቱ ተደልድሎ ሜዳ የተሠራ ሲሆን ለሕፃናቱ መጫወቻ አመቺ ይሆን ዘንድ ሣር ስለተተከለበትና በሚገባ ስለታጠረ ከአለፉት ዓመታት ይልቅ በዘንድሮው ዓመት ሕፃናቱ በሚገባ ለመዝናናትና ለመጫወት መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸዋል ። ይልቁንም በዚሁ መዋለ ሕፃናት ከሚያስተምሩት መምህራን ከሌሎቹ ወደ መዋለ ሕፃናት መምህራን ማሠልጠኛ ተቅዋም ተልከው ስለመዋለ ሕፃናት ሥነ ሥርዓት ፣ ሕፃናትን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ፣ስለሕፃናትአጠባበቅናአያያዝ አጥንተውየተመለሱ በመሆናቸው በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚታየው የሥራ አያያዝ በሚያኰራ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ። ለሕፃናቱ የሚደረግላቸው እንክብካቤም ከሌሎቹ ተመሳሳይ መዋለ ሕፃናት ጋር ሲነጻጸርና ከሚከፈለው ወርኃዊ ክፍያ ጋር ሲመዛዘን አገልግሎቱ በሚያስደስት ሁኔታ ላይ ነው ።

እንደ ዲያቆን ከፍ ያለው አባባል ሕፃናቱ ተገቢ ቁርስ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብላቸው መደረጉና በአንድ ክፍል ውስጥ ቢበዛ ከ፵ የማይበልጡ ሕፃናት እንዲመደቡ በመደረጉ መምህራኑ እያንዳንዱን ሕፃን በቅርብ ለመረዳትና ለመቆጣጠር ስለሚያስችላቸው ይህ መዋለ ሕፃናት ከሌሎች ተመሳሳይ መዋለ ሕፃናት የተሻለ ውጤት ያሳየ መሆኑን ለማወቅ ይቻላል ሌላው ደግሞ ተገቢ የሆኑ የትምህርት መሣሪያዎች ና የምግብ ቁሳቁሶች መኖራቸው ሲሆን ይህ ሊሟላ የቻለው ካቴድራሉ ከአንዳንድ ዓለም ዓቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ባደረገው መጻጻፍ በተገኘው ርዳታ መሆኑ ተረጋግጧል ።

መዋለ ሕፃናቱ የሚገኝበት ቦታ ማዕከላዊ ከመሆኑ የተነሣ ብዙዎች ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስገባት በየጊዜው የሚጠይቁ ቢሆንም ጥራት እንጂ ብዛት ብቻ ስለማይፈለግ ክፍሎች እስኪጨመሩ ድረስ የሕፃናቱ ቁጥር ለጊዜው ከ፻፶ እንዳይበልጥ መደረጉንም ከዋናውጸሐው ጋር ባደረግነው ውይይት ለመረዳት ችለናል ፤ ቀጥሎም መምህራኑን አንድ ባንድ አነጋግረን ነበር ። በዚሁ ጊዜ ከመምህራኑ መካከል ከወ/ት የኋላአሸት ደመቀና ከእማሆይ እህተ ማርያም ገብረ ሥላሴ ባገኘነው ማብራሪያ መሠረት የዓፀደ ሕፃናቱ ሥራ አመራርና ይዞታ የሚከተሉትን የያዘ ነው ።

### ሀ/ የክፍሉ አመዳደብ

በ"ሀ" ክፍል በጣም ሕፃናት የሆኑ ጀማሪዎች

በ"ለ" ክፍል በዕድሜም ሆነ በትምህርት ሻል ያሉት

በ"ሐ" ክፍል ወደ 1ኛ ክፍል ለማዛወር በመዘጋጀት ላይ ያሉ

በ"መ" ክፍል በመዋለ ሕፃናቱውስጥ ከሌሎች በጣም የተሻሉና ወደ 1ኛ ክፍል ለመዛወር ዝግጁዎች የሆኑ ናቸው። በዚሁ ምድብ መሠረት በሚከተለው ሁኔታ የትምህርቱ ፕሮግራም ይካሄዳል ።

### ለ/ የትምህርት ፕሮግራም

1. የፊደል ጥናት፡- በቅርፃ ቅርፅ መልክ የተዘጋጁ ፊደሎች ስላሉ እነዚህን በማየትና በማጥናት የፊደሎችን መልክ እንዲያውቁ ጥረት ይደረጋል ። ፊደ



www.ethiopianorthodox.org

ሎቹን ካጠኑ በኋላ በፊደላቱ ቃላትን እየጻፉና እያነበቡ እንዲለማመዱ ይደረጋል ።

፪. የሂሳብ 'የቁጥር ትምህርት በዚህ ትምህርት እንደዚሁ በቅርፃ ቅርፅ መል ክ የተዘጋጁ ቁጥሮች ስላሉ በነሱ አማካይነት እንዲማሩ ይደረጋል ። በተለይ አንዱን ቅርፅ ከሌላው ጋር በማገጣጠም አንድን ቁጥር ለመሥራት የሚያስችሉ ቅርፆች ስላሉ በዚህ ዘዴ በመጠቀም አኃዞችን በቀላሉ ይለማመዳሉ ።


3- መዝሙር፦ መንፈሳውያን ዓለማውያን መዝሙሮችን እየዘመሩ እንዲዝናኑ ይሆናል ።

4. የንጽሕና አጠባበቅ ፦ በዚህ ጥናት ስለሰውነታቸውና ስለአካባቢያቸው ንጽሕና ያጠናሉ ። በዚሁ መሠረት አንዳንድ ጊዜ ግቢያቸውንና የመጫዎቻ ሜዳቸውን እያፀዱ በተግባር ላይ እያዋሉት ይታያሉ ።

5. ስፖርት ፦ በዓቅማቸው መጠን የ ሰውነት ማጠንከሪያ ስፖርት እየሠሩ ሰውነታቸውን ያጠነክራሉ ።

፮. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በዚህ ፕሮግራም ለሕፃናት የሚመጥኑ ዋና ዋና ጥቅሶችን እንዲያጠኑ ያደርጋል ፤ ለምሳሌ እናትና አባትን ማክበር እንደሚገባ እርስ በርስ መፋቀር አስፈላጊ መሆኑን ስለትሕትና የመሳሰሉትን እያጠኑ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ምክር ይሰጣቸዋል ።



ዐመዋል ሕፃናት የሚያስተምሩ መምሕራን ከሕፃናት ጋር

፯. የሥዕልና የጽሕፈት ልምምድ በ ተለይ ወደ ፩ኛ ክፍል ለመዛወር በዝግጅት ላይ ያሉት በዚህ በኩል ጠበቅ ያለ ክትትል እንዲያደርጉ ይደረጋል ።

፰. የሽርሽር ክፍለ ጊዜ ፦በዚህ ፕሮ ግራም በአካባቢያቸው ወደሚገኙት አ መቺ ቦታዎች እየተዘዋወሩ የሰልፍንና የሕብረት አረራመድን ይለማመዳሉ።

፲. ሥርዓተ ጸሎት፦ ወደ ክፍል ከ መግባታቸው በፊት ሁልጊዜ ጸሎት ይ ጸልያሉ ብሔራዊ መዝሙርም ይዘምራ ሉ የጸሎት ፕሮግራሙም ወደ ክፍል ከ መግባታቸው በፊት ብቻ ሳይሆን በም ግብ ጊዜም ይጸልያሉ ።

፲፩. የምግብ ሁኔታ፦ ሕፃናቱ ቁርስና ምሳ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ከፋፋ የተዘጋጀ ገንፎ ይቀርብላቸዋል ። ከዚህ በተረፈ ምሳቸውን ይዘው ስለሚመጡ በሚመገቡበት ጊዜ የምግዚቶቹ ቁጥ ጥር ሳይለያቸው በአመቺ ቦታ እንዲመ ገቡ ይደረጋል ።

ሐ/ የማስተማሪያ ዕቃዎች

፩/ ከልዩ ልዩ ነገሮች የተሠሩ የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆች በነዚህ ቅርፃ ቅር ፆች መሠረት አራት ማዕዘንን ሦስት ማ ዕዘንን አስኳርንና ክብን ወዘተ የመሳሰ ሉትን ሁሉ በዓይናቸው እያዩ በእጃቸ ው እየዳሰሱ እንዲማሩ ስለሚደረግ በ ዚሁ መሠረት በልምምድ ጊዜ የሚጠቀ ሙባቸው ቅርፃ ቅርፆች አሉ ።

፪/ ፊደላት በዓይነታቸው የተግሉባ ቸው ቅርፆች አሉ

፫/ ቀለማትን ለመለየት የሚያስችሉን ዊ ፡ጥቁር ፡ቀይ ፡አረንጓዴና ብጫ ሌሎ ችንም ቀለማት የተቀቡ በርከት ያሉ ቅ ርፃ ቅርፆች ይገኛሉ ።

እንዲሁም ኳሶችና የመሳሰሉት መጫ ወቻዎች ስላሉ በነዚሁ መጫወቻዎ ች ሕፃናቱ ከመደሰታቸውም በላይ እነ ዚህን እየገጣጠሙና እያንከባለሉ ስለ ሚጫወቱ ያላወቋቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል ።

መ/ የመሥሪያ ዕቃዎች

አካፋ ፡የውኃ ማጠጫ ባልዲ ፡መኮት ኮቻ ፡ገምና ሌሎችም የእርሻ መገሪያዎ ች ስላሉ በዚሁ መሠረት በዓቅማቸው መሠረት ስለ እርሻ እንዲያስተውሉ ይ ደረጋል ።

ረ/ የሰዓት ፕሮግራም

ከላይ የተዘረዘሩት ፕሮግራሞች የሚ ካሄዱት ከሰዓት በፊት ከ፪ከ፵፭እስከ፮ ከሰዓት በኋላ ከ፰ከ፴ እስከ ፱ከ፴ ሲሆን በዚህ ትምህርት ቤት መዋለ ሕፃናት ገብተው ለመማር ከ፫-፮ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናቸው አብዛኛዎቹ ግን ከ፬እስ ከ ስድስት ዓመት የሚሆኑ መሆናቸው ን አረጋግጠናል ።

## እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

ከገጽ ፮ የዞረ

እንደሆነ መረዳት ይቻላል ። መን ፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል ፍጹም መልክዕ ያለው ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ በክብር በሬቃድና በአገዛዝ እኩል ነው ። በተለየ ከዊንም ለራሱ ሕይወት ሆኖ ለአብና ለወልድ ሕይወት ነው ። ለሰዎች ም ወሃቢ ሕይወት ነው ። በመሆኑም በዓለም ያለች ቤተ ክርስቲያን በመን ፈስ ቅዱስ የተመሠረተችበትን ዕለት ለማስታወስ መድኃኒታችን ክርስቶስ በተነሣ በሃምሳኛው ቀን በዓለ መንፈስ ቅዱስን ታከብራለች እንዲሁም እያለች ትመሰክራለች ።

"ከአብ በሠረፀ ጌታ ሕይወት ሰጭ በሆነ ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለትና በሚመሰገን በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን"



የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማር ያም ልደት በቅዱሳት መጻሕፍት ይል ቁንም በመጻሕፍተ ብሉያት በትንቢት ና በምሳሌ በሰፊው ተጽፎ ይገኛል ሙ ሴ ኮሬብ በተባለው ተራራ በጎቹን አሰ ማርቶ ሲጠብቅ ሳለ አንድ አስደናቂ ራ እይ አይቶአል ይኸውም ነበልባል ከሐ መልማል ጋር ተዋህዶ ነበልባሉ ሐመል ማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉ ነበልባ ሉን ሳያጠፋው አይቶአል ዘጸአ ፫፥፪ይህ ራእይ የመለኮትና የትስብእት ተዋህዶ ምሳሌ ነበር ነበልባል የመለኮት ሲሆን ሐመልማል ደግሞ የእመቤታችን ምሳ ሌ ነው ።

ይህ ሙሴ ያየው ራእይ የእመቤታች ን ምሳሌ መሆኑንም ሲገልጽ ቅዱስ ኤ ፍሬም እሳት ሳያቃጥላት በበረሐ ሙሴ ያያት እንጨት ድንግል ማርያም ንት መ ስላለች ሲል አትልቶ ተናግሯል/ኤፍ፬፡፩/ እንግዲህ ሙሴ ያየው ራእይ የእመቤታ ችን ልደት ብቻ ሳይሆን የጌታችን የኢ የሱስ ክርስቶስም ተዋህዶ ጭምር እንዳ የ እንረዳለን ከሙሴ በኋላ የተነሱ ቅዱ ሳን ነቢያትም የእግዚአብሔር መንፈስ በገለጸላቸው ረቂቅ ምሥጢር ስለ እመ ቤታችን ልደት በየትንቢታቸው የተና ገሩ ብዙዎች ናቸው ለምሳሌ በየዋህነቱ ና በገርነቱ ልበ አምላክ የሚል ቅጽል ያገኘው ዳዊት የእመቤታችንን ልደት በምሥጢር ሲገልጽ መሠረቶቹ በተቀ ደሱ ተራሮች ናቸው ከያቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆዎች ይወዳቸዋልና መዝ.፹፮፥፩ብሏል ነቢዩ ዳዊት በዚሁ ሳይገታ ያንን በምስጢር ተናግሮት የነበረውን አጉልቶ አብራር ቶ ሲናገር እግዚአብሔር ጽዮንን መር ጧታልና ማደርያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና ይህች ለዘላለም ማረፊያ ዬ ናት መርጫታለሁና በዚች አድራለ ሁ» ብሏል ፻፴፩፥፲፫ ከዚህ በላይ እርስ ዋ ከተወለደች በኋላም የአብ አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥ ቶ ባሕሪዋን ተዋህዶ በማህፀንዋ እንደ ሚያድር ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁና በሚለው አረፍተ ነገር አብራርቶ ተናግሯል ።

የእመቤታችን ልደት እነ ዳዊት ብቻ ተናገረውት አልቀሩም ነቢዩ ኢሳይያ ስም ከዕሴይ ግንድ ብትር ይወጣል ከሥ ሩም ቁጥቋጦ ያፈራል ፡፡ኢሳ.፲፩.፩ ብ ሏል ። እንዲህም ማለት በበትር የተመ ሰለችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል የተ ባለውም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ መሆኑን ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ድጓ በተባለው ድርሰቱ በ ትር ከዕሴይ ሥር ትወጣለች አበባም ከ እርስዋ ይወጣል በትርዋም የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌስትሆንከእርስ

# ልደታ ለማርያም

ዋ የወጣው አበባ ደግሞ የእግዚአብሔ ር ወልድ ምሳሌ ነው» ሲል ተርጉሞ ታል ።

ነቢዩ ሕዝቅኤልም ስለ እመቤታችን ልደትና ሁኔታዋ እንዲህ ሲል ተንብየ ዋል " ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከተ ው በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር ይህ በ ር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም



እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

ሰውም አይገባበትም የእሥራኤል አም ላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ሕዝ ፵፬፥፪ ይህም ሕዝቅኤል 'ያየው/ የተ ናገረው ትንቢት ምሥራቅ የተባለችው ቅድስት ድንግል ማርያም ይህ በር ተዘ ግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም የተ ባለውም የማህተመ ድንግልናዋ ምሳሌ መሆኑንና የእመቤታችን ማህተመ ድ ንግልና እርሱን ከመጽነስዋ አስቀድሞ እርሱንም ከጸነሰችው በኋላ እርሱን ከ መውለድዋ አስቀድሞ እርሱንም ከወ ለደችው በኋላ በድንግልና እና በንጽሕ ና ጸንታ የመኖርዋን ያስገነዝበናል ይህ ንንም የተነገረውን ትንቢት የተመሰለው ን ምሳሌ መሠረት በማድረግ የእመቤ ታችንን ልደት አስፋፍተው የተናገሩ ብ ዙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አሉ ።

የነቢያትን ትንቢትና ምሳሌ መሠረ ትም በመያዝ ከሊቃውንቱ አንዱ አባ ሕርያቆስ የእመቤታችንንጥንተ ልደት ሲናገር ድንግል ሆይ ነቢያት ትንቢት የተናገሩልሽ ምሳሌ የመሰሉልሽ አንቺ ነሽ ብሏል /ቅዳ.ማር/37 ፡

ኢያቄምና ሐና /ብዝኀ ወተባዝኀ ወምልእዋ ለምድር /ብዙ ተባዙ ምሬት ንም ሙሏት" ዘፍጥ ፩፡፳፰ በሚለው አም ላካዊ ትእዛዝ መሠረት በሕግ ከተጋቡ በኋላ ልጅ አጥተው ሲያዝኑና መራራ ልቅሶንም ሲያለቅሱ መኖራቸው የሚ ታወስ ነው መቸም እንደሚታወቀው አንድ ሰው በዚህ በምድራዊ ዓለም ዓለ ሙን እስከ መግዛት ድረስ ከፍ ያለ ክብ ርና ስፍር ቁጥር የሌለው ሀብት ቢኖረ ውም ስሙን የሚያስጠራ ተተኪ ዘር ከሌለው ፍጹም ደስታ እንደማይኖረው እርግጠኛ ነው እንዲያውም ያ የሰበሰ በው ሀብት ከፊቱ ተደቅኖ እያየ ይህ ሀ ብትና ንብረት ለማን ሊሆን ነው ?ማን ይወርሰዋል በሚል ሐሳብ የሌሊት እን ቅልፍ እንደሚያሳጣው ብዙ ሀብት አግ ኝተው ልጅ በማጣት ሲያዝኑና ሲያለቅ ሱ የሚኖሩትን ሰዎች መመልከት በቂ ምስክር ነው ።

ሕንቃር የተባለ ፈላስፋ ም ልጅ ስለ ሌለው ሰው ሲናገር "ልጅ የሌለው ሰው በመንገድ ዳር የበቀለችና ፍሬ የማይገ ኝባት መንገደኞች 'ነጋዴዎች/ ቅጠሏ ን እየዘነጠፉ ቅርንጫፎችዋንም እየቆረ ጡ የእግራቸውን ትቢያ የሚያራግፉባ ት የበረሐ እንስሳት የሚበሏዋትንዛፍይ መስባል ብሏል ። አንጋረ ፈላስፋ ፲፮ ገጽ ፎ፫ ።

በገጽ ፳፫ ይመለከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብ

በከፍያለው መራሂ

ታሪክ መስተዋት ነው የረቀቀ ውን አጉልቶ የተረሳውን መዝግቦ ያሳ ያል ቤተ ክርስቲያንም በህብረተሰብእ ዘንድ ሀልውናዋ በታሪክ ዓምድ ላይ ከ ተመዘገበበትና ከተከሠተበት ጊዜ ጀም ሮ እስከአሁን ድረስ በእውቀት ፣በሥል ጣኔና በማህበራዊ ኑሮ ለኅብረተሰብእ ያበረከተችው አስተዋጽኦ ምን ነበር ? ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ የነበራ ቸውና ያላቸው ትውውቅና ግንኙነት እንዴት ነው ?

ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊት ድር ጅት እንደመሆንዋ መጠን የመጀመሪ ያ ሥራዋ አምልኮተ እግዚአብሔርንለኅ ብረተሰብእ ማስተዋወቅ ነው ። በሌላ አነጋገር ለፍጡር ፈጣሪ እንዳለው መስ በክና ማስተማር ነው ።

በአንጻሩም "ጥረህ ግረህ በላብህ ወዝ እደር" የሚለውን መለኮታዊ ትእዛዝ ለ ኅብረተሰብእ መሻሻልና ደኅንነትያለ ዕ ረፍት በትጋትና በንቃት ስታስተምር ኑ ራለች ፣አሁንም ታስተምራለች ።ይህም ይታወቅ ዘንድ

ቤተ ክርስቲያን በእውቀት ዓለም በ ምርምርና በስነ-ጥበብ ረገድ ኅብረተሰብ እን ስታስተምርና ስትመራ፣ብራናዳምጣ ብርዕ ቀርጾ፣ቀለም አዘጋጅታ ስነ-ጽሑፍ ን በመጻፍ ሙዚቃን ቋንቋንና ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ ስታስተላል ፍ ኑራለች ። የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላ ማ ኅብረተሰብእበመንፈሳዊም ሆነበሥ ጋዊ ሕይወቱ ጤናማ እንዲሆን ነው ። ቤተ ክርስቲያን ኅብረተሰብእበመንፈ ሳዊ ሕይወቱ ሕያው ይሆን ዘንድክርስ ቶስን የምትሰብክለትን ያህል ፣በሥጋ ዊ ሕይወቱም የተጓደለውን ጤንነቱ ን ለማስተካከል ዕፅዋትን በመቀመም ፣ ያበጠውን በማፍረጥ ፣የጐረበውን በመ ላጥ መድኃኒት ቀምመው የሚፈውሱ ሊቃውንት እንደነበሩ አት አይዘነጋም ፣ ዛሬም ቢሆን ያለ ነው ። ይህም ቤተ ክ ርስቲያን ለኅብረተሰብእ መሻሻል ግንባ ር ቀደም መሪና አስተማሪ እንጂ የሥል ጣኔ እንቅፋት አለመሆኗን በጉልህ ያሳ ያል።በእርግጥ በቤተክርስቲያን ትምህ ርት የሥልጣኔ መጀመሪያ ፍጡር ፈጣ ሪውን ተመራምሮ ሲያውቅና ሲረዳ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ተብሎ ተጽፏልና ፣ ይህም ሰው ከሚይዛቸውና ከሚነዳ ቸው ደመ ነፍስ እንስሳት ተለይቶ ልዩ ነቱና አስተዋይነቱ የሚታወቅበት መ ንገድ ነው ። ይህ ደግሞ የማወቅ የመ ራቀቅንና ስነ-ፍጥረት ን የመመርመር በርን ከቶ አይዘጋም ።

ከኅብረተሰብእ የታሪክ ማህደር እን ደምንረዳው ቤተ ክርስቲያን ፍትህን ነፃ ነትን ፣ግብረ-ገብነትን ፣ጠቃሚ ሥር ዓትን ለኅብረተሰብእ ስታስተምር ኑራ ለች ። አሁንም በማስተማር ላይ ትገኛ ለች ። እንግዲህ "ጥርስና ከንፈር ቢ.ተባ በር ያምር" እንዲሉ ህብረተ ሰብእ ም ይህን በመረዳት ቤተ ክርስቲያንን አቅፎና ደግፎ ይይዛታል ።

ቤተ ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮ የቤተ ክርስቲያን ህልውና በኅብረተሰ ብእ መካከል ከተገለጸበት ጊዜ ጀምሮ ፍቅርን ፣ ሰላምን ፣መከባበርንና መረዳ ዳትን " ሁለት ያለው አንዱን ለሌላው ይስጥ" እያለች በማስተማር ለኅብረተ ሰብእ የማህበራዊ ኑሮ ጮው ሆና ኑራ ለች ።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲ ያናችን ከቀድሞ ጀምሮ ለኅብረተሰብኡ ርኅራኄን ፣መረዳዳትን ፣ድሆችንና በሽ ተኞችን መርዳት እንግዳ መቀበልን ስ ታስተምር ኑራለች ፣ኢትዮጵያውያንም የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በጸጋ ተ ቀብለው ሲሠሩበት ኑረዋል ። ይህም ተ ግባር ከክርስትና ሃይማኖት የተገኘ ጠ ቃሚነቱ ከፍያለ ሲሆን አንድ አንዱ ደ ግሞ ከጥንት ዘመን የመጣ ከኢትዮጵያ ውያን ደም ጋርየሠረጸእንግዳመቀበልና ማስተናገድን የመሳሰለው ሰብአዊ ርኅ ራሄ ነው ። ይህንም ጥንታውያን የሆኑ ዕርዓውያን "ኢትዮጵያውያን ርኅራሄአ ቸውእንደፈጣሪአቸውነው"ሲሉ አመስ ግነው ጽፈዋል ። የዛሬው ጊዜ ሥራችን ከማህበራዊ ኑሮአችን ጋር ሲመዛዘን ጥ ንታውያን አባቶቻችን በሥልጣኔው ከ ፍ ያሉ እንደነበሩ ማኅበራዊ ሥራቸው ግልጥ ሆኖ ያስረዳል ወገንንም ያኮራል።

ከዚህ ላይ ማኅበራዊ ኑሮ በመሠረቱ ክርስቲያናዊ ትምህርት ነው ፣ክርስቲ ያናዊ ትምህርትም ማኅበራዊ ኑሮ ነው እንጂ አንዱ አንዱን የሚያፈርስበት ወይም ተቃራኒ የሚሆንበት ነገር የለው ም ። ምክንያቱም የሁሉም መሠረት ወ ይም መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ ነ ውና ከክርስትና በፊት አይሁድና ሳም ራውያን አይገናኙም አይተባበሩም ነ በር ፣ዕብራውያንና አረማውያንም እን ዲሁ አይስማሙም አይተባበሩምነበር፣ ከዚህ ጋር እያንዳንዱ ነገድ በበኩሉ የተ ለያየው በአንድ መንግሥት የሚተዳደ ረው ሕዝብ ሳይቀር ብዙ ግንኙነት አል ነበረውም ፣ስለዚህም አይረዳዳም ፣አይ ተባበርም ነበር ። በዚህም ምክንያት የ አንዱ መውደቅ ለአንዱ ጽድቅ እየመሰ ለው የሰው ልጅ በሰው ልጅ ሲቀልድ ይኖር ነበር ። በክርስቶስ ትምህርት ግን ይህ ሁሉ መንፈስ ጠፋ ሁሉም በእ ርሱ መንግሥት እንደሚተዳደር በርሱ ም ዘንድ ይህ ዓረማዊ ነው ይህ ግንዕብ ራዊ ነው የማለት ልዩነት ሳይኖርበት ፣ በርሱ ያመነ ሁሉ እንደሚድን የሰው ልጅ ሁሉ የርሱ ም ቤተሰብ እንደሆነ በ ቃልም በሥራም አስረድቷል ።

ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ህብረተ ሰብኡ በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲድን እንዲሁም ደስተኛ ኅብረተሰብእ እንዲኖር ቤተ ክርስቲያ ን ዛሬም ሆነ ወደፊት የማህበራዊ ኑሮ ቅመም የሆነውን ሕገ ወንጌል ታስተም ራለች የሰላም ፣የፍቅርና የመረዳዳትን የምሥራች ትሰብካለች ።

የቤተ ክርስቲያን ም አገልግሎት ለኅ ብረተሰብእ በዚህ ብቻ አይወሰንም ።

በገጽ ፳፩ ይመልከቱ



# ፍልሰተ አጽሙ ለተክለ ሃይማኖት

የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ት አባታቸው ጸጋ ዘአብና እግዚእ ኃረያ ይባላሉ ። እነሱም ልጅ የሌላቸው መካ ኖች ስለነበሩ እግዚአብሔር ልጅ ይሰጣ ቸው ዘንድ በጾም በጸሎት ይለምኑ ነበር ። እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ የተባረከ ልጅ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ሰጣቸው ። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ካደጉ በኋላ ፳፭ ዓመት ሲሆናቸው እየተዘዋወሩ በቡልጋና በም ንጃር በሸንኮራም ያስተምሩ ጀመር ። ከዚያም አልፈው የጉራጌን አገር እያስ ተማሩ ወደ ወላይታ ወረዱ ይኸውም ወላሞ ይባል የነበረው አገር ነው ። ያን ጊዜ ግን ይባል የነበረው ሀገረ ዳሞት ነበር ። ያን ጊዜ በወላይታ የነበረው አገረ ገዢ ሞተለሚ ይባል ነበረ ። እሳ ቸውም ሞተሎሚን መክረው አስተም ረው አሳምነው አጠመቁት ። ከዚያም ፲፪ ዓመት ከተቀመጡ በኋላ ተመልሰው ወደ አማራው አገር መጡ ። ከዚያም አልፈው ወሎ ውስጥ አማራ ሳይንት ሂደው ከአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ጋስጫ ገብተው ፲ ዓመት ረድተዋል ። ከዚያም አልፈው ወሎ ውስጥ ሐይቅ ተሁለደሬ ከሚባለው (ወረዳ) ከአባ ኢየሱስ ሞዓ ገዳም ገብተው እንደዚሁ ፲ ዓመት ሲረዱ ኖረዋል ። ከዚያም ተነሥተው ወደ ትግራይ ሂደው ከአቡነ አረጋዊ ገዳም ደብረ ዳሞ ገብተው ከረዱ በኋላ ከአባ ዮሐኒ ዘንድ መዓርገ ምንኩ ስና ተቀበሉ ። ከዚያም ፲፪ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ ተነ ሥተዋል ። ከዚያም ሂደው ፀዓዳ አምባ ከሚባለው ገዳም ገብተው ሐማሴኖች (ኤርትራውያን) እምባ ሥላሴ ከሚሉት ደረሱ ። ከዚያም በጣም ያረጁና ያፈጁ ሰውነታቸው የደቀቀ እርጅና የተጫና ቸው አረጋውያን አበው አባቶች አግኝ ተዋል ። እሳቸውም ከእነሱ ተባርከው ተክለ ሃይማኖትም እነሱን ባርከዋቸው ተቀምጠው ሳለ ከዚህ በኋላ መነኮሳቱም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ሲነሡ አባ ቀልጠፍ ብለህ በቶሎ ተመለስ ብለው ለመኗቸው ከዚያም ተ ነሥተው የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ሔደዋል ። ጥንት ኤርትራ በዓረብኛ ቋንቋ ባሕረ ሱፍ ፣ በአማርኛ ቀይ ባሕር ነበር ። ዛሬም ይባላል ። እሳቸው የኤርት ራን ባሕር ተሻግረው ወደ ኢየሩሳሌም ወርደዋል ።

ከዚያም በኋላ ጌታ የተወለደበት ቤተ ልሔምን የተጠመቀበት ዮርዳኖስን የተሰቀለበት ቀራንዮን የተቀበረበት ጎልጎታን ፣ ጌታ ያስተማረበትንና ታም ራት ያደረገበትን ይህን የመሳሰሉትን ወይም አባ ብንያሚ ይባል ነበር ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ከእሱ ዘንድ በካይሮ (በእስክንድርያ) ለመቀመጥና ለመኖር ቢያምራቸው ፓትሪያርኩም ወደ አገርህ ሂድ ክፍልህ ኢትዮጵያ ናትና አላቸው ። ከዚያ በኋላ ከግብፅ ማለት (ከካይሮ) ተነሥተው ተመልሰው ወደ ሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተ ዋል።መጥተውም ምድረ ግራርያ የሚ ባለውን አገር እያስተማሩ ለገዳምነት መርጠውታል ። ከዚያም ሆነው እያስተ ማሩ በጾም በጸሎት በስግደት በልዩ ልዩ ትሩፋት ተወስነው ሳሉ ብዙ ደቀ መዛሙርት አፍርተዋል ። ከእነዚሁም



ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መጀመሪያ አጽማ ቸው አርፎበት በነበረው መካነ አሰቦ በተባለው ቦታ እንደጸለዩ

ቦታዎች ጐብኝተው ወደ ግብፅ ወርደው ካይሮን እስክንድርያን ሲሐትንና ገዳመ አስቄጥስን ሁሉ ጐብኝተዋል ። ያን ጊዜ የነበረው የእስክንድርያው ፓትር ያርክ አባ ሚካኤል የሚባለው ነበረ ።

አንዱ አቡነ ፊልጶስ ናቸው ። ፲፪ቱን ንቡራነ እድ ሁሉ ያገኙ ከዚሁ ገዳም ነውና ።

የአቡነ ፊልጶስ አገራቸው ሰላሌ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ወርኃ ግንቦትና ከንቱ አምልኮት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አከፋፈል አንዱ ዓመት በአራት ክፍሎች ተመድቦ ይነገራል እነርሱም ዘመነ መፀው ፤ ዘመነ ሐጋይ ፤ ዘመነ ፀደይና ዘመነ ክርምት ናቸው

ግንቦት ከተጠቀሱት ክፍሎች ዘመነ ፀደይ ተብሎ ከተሠየመው ውስጥ ይመደባል ። የግንቦት ወር አየሩ እጅግ በጣም የሚሞቅበት ፤ ፀሐዩ የሚጠርበት ሲሆን ደመናት በጠፈረ ሰማይ አልፎ አልፎ የሚታዩበት ፤ ገበሬዎች ለመዘ ነም ፤ የሚጀምሩበት ፤ ቅርንጫፎቻቸውን እንጨብርረው ቅጠሎቻቸውን እርግፍ አድርገው ዕርቃናቸውን በመቆም ወርኃ ሐጋይን ያሳለፉት ዛፎች አጨፍጭፈው የሚታዩበት ነው ።

እንዲሁም አትክልት ከጓሮች ፤ አዝርዕት ከበሰላዎች ራሳቸውን ብቅ አድርገው የሚታዩበት ፤ እንስሳት ጨሌ ልሰው ፤ ቅጠል በጥሰው በመደሰት ለመበረቅ የሚጀምሩበት ይህ ወር ስለሆነ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት የደስታ ጨላጨል ነው ለማለት ያስደፍራል ።

በአውሮፓ ደግሞ ግንቦት የክረምቱ ዘመን አልፎ ፤ በመሬት ላይ ተኝቶ ለብዙ ጊዜ የቆየው በረዶ ማሙቶ የአበባው ወራት የሚጀመርበት ስለሆነ የመጀመሪያ በጋ እየተባለ በአንዳንድ ሀገሮች ይጠራል በዚህ ወር ምድር በአበባና በልምላሜ ተውጣ ፤ ጋራዎችና ሸንተረሮች በቅጠልና በሣር ተሸፍነው ይታያሉ ፤ እንዲሁም አትክልትና አዝርዕት አብበው ፤ አሽተውና አፍርተው የሚታዩበት ስለሆነ አውሮፓውያን አስደሳቾች ወራቶች ብለው ከሚጠሯቸው ወሮች የመጀመሪያውን ከፍተኛ ደረጃ የያዘው ይህ የግንቦት ወር ነው ።

በተጨማሪም በዚሁ ወር በበረዶው ምክንያት ተዘግተው የነበሩት የምግብ ቤቶች /ሆቴሎች/ ፣ቤተ መጻሕፍት፣ መዋኛዎችና ሌሎችም አስደሳች የሆኑ ልዩ ልዩ ድርጊቶች በሚገባ ተዘጋጅተው አገልግሎታቸውን መስጠት ይጀምራሉ ፣ወሩ እጅግ በጣም አስደሳች ስለሆነ ዓመቱን በሙሉ በትጋትና በንቃት ሲሰሩ የከረሙ ሠራተኞች የዓመት ዕረፍታቸውን የሚጠይቁት በዚህ ወር ነው ።

የግንቦት ወር በሀገራችንና በውጭ ሀገር ያለውን ጠባይ በመጠኑ ተመልከተናል እስኪ ደግሞ በዚሁ ወርና በሌላም ጊዜ ስለሚፈጸሙት ከንቱ የሆኑ አምልኮቶች እንመልከት ።

የሌሎች ሀገሮች ሰዎች እንደኛ ሀገር የግንቦትን ወር ተጠግተው አምልኮ ባዕድን አይፈጽሙም በሀገራችን ግን በሌሎች ወራት ከሚፈጸሙት አምልኮ ባዕዶች በግንቦት ወር የሚፈጸሙት በርከት ያሉ ሆነው ይታያሉ ከሚፈጸሙትም ልዩ ልዩ አምልኮ ባዕዶች አንደኛው ጋብቻን የተጠጋ ነው ።

አንዳንድ ሰዎች በግንቦት ወር የሚፈጸም ጋብቻ መሠረቱ ሊጸና አይችልም ፤ ለሴትየዋ ወይም ለሰውየው ጤና ስለማይሆን አብረው ለመኖር ፍላጎት አይኖራቸውምና ጋብቻቸው አይጸናም ፣ይፈርሳል ! እያሉ በሐሠት ይተነብያሉ ።

ሌሎች ሰዎች ደግሞ የግንቦት ወር አየሩ ሞቃት ፣ነፋሱ ደረቅ በመሆኑና ቁስልም ስለሚበረታበት ለተጋቢዎቹ በጣም አደገኛ ነው ። በተለይ ለሴቲቱ ጤና እጅግ በጣም አስጊ ነው ይላሉ ። እንዲሁም ከግንቦት ወር መጀመሪያ እንሥተው እስከ መጨረሻው ድረስ ዶሮ ፣በግ ፣ኮርማ ፣እያረዱ ቡናና ቆሎ ፣እየቆሉ ፣ቂጣ እየጋገሩ ፣ከታላቅ ዛፍ ሥር ያም ባይገኝ በቤት ታዛ ተሰብስበው ተመግበው የተረፈውን ወደቤት ሳያስገቡ በመንገድ ላይ ይበታትኑታል ወደ ቤት የገባ እንደሆነ ከቤቱ ውስጥ ተባይ ይፈጠራል ፣ጉንፋን ፣በሽታ ይሆናል እያሉ በከንቱ አምልኮ የሚመሩ ሰዎች አሉ ።

በግንቦት ወር ከሚፈጸሙ አምልኮቶች ጥቂቶቹን ጠቀስኩኝ እንጂ ከንቱ የሆኑ አምልኮቶቹ የሚፈጸሙት በግንቦት ወር ብቻ ነው ለማለት አይደለም ፤ ፈጻሚዎችም ኢትዮጵያውያን ብቻ አይደሉም በየትኛውም ዓለም ልዩ ልዩ አምላኪዎችና ተመላኪዎች ነበሩ አሁንም አሉ ርዝራዣቸው አልጠፋም ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከእሥራኤላውያን በስተቀር የቀረው ሕዝብ ሁሉ ከአባቱ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ራሱ የወደደውንና የመሰለውን ልዩልዩ የጣዖትና የአስማት አምልኮ ይዞ ይኖር እንደነበር በታሪክ ይነገራል፡ከዚህም የተነሣ ዓለሙ በጠቅላላ ከአምልኮ ጣዖት የተላቀቀበት ዘመን አልነበረም ።

በአገራችን በኢትዮጵያ በአብርሃና በአጽብሃ ዘመን በ፫፻ ዓ'ም.ላይ የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ በስተሰሜን ክፍል እጅግ በጣም ተስፋፍቶ ነበር ። እንዲሁም በ፲፬፻፹፮ ዓ.ም. የነገሡት አፄ ዘርአ ያዕቆብ ለክርበትና አምልኮ ቀናዒ ስለነበሩ በመላው ኢትዮጵያ ተንሰራፍተው የነበሩትአምልኮቶችለምሳሌ የአስማት ፣የጥንቆላ ፣የሟርት የከንቱ አምላኮቶች ተግባሮች ሁሉ በጠቅላላ እንዲጠፉ በትዕዛዝ ም ፣በስብከትም ፣ መጣራቸውን ከታሪካቸው ለመረዳት ይቻላል ይሁን እንጂ ለጊዜው ጋብ ያለ መስሎ ቢታይም ፈጽሞ ሊወገድ ሳይችል ቀርቷል ።

ወደሌሎች ሀገሮችም እርመድ ብለን ታሪክ ስንመለከት ከከንቱ አምልኮ ነፃ ሆነው አናገኛቸውም ለምሳሌ የግብፅ ነገሥታትና ሕዝብ ዋነኛው አምልኮአቸው በፀሐይ ነበር ፀሐይንም ሲያመልኩ ልዩ ልዩ መልክና ሥያሜ ሰጥተው ከሦስት በመከፈል ነበር ።

ይኸውም አንደኛ ሖሩስን ወይም አር የጎሕ ፀሐይ ፣የንጋት ፀሐይ/ሁለተኛ ዐይንን የሚያንፀባርቅ የቀን ፀሐይ፣ሦስተኛ የማታ ወይም የጥልቀት ፀሐይ በማለት ሲሆን እነዚህንም በልዩ ልዩ ቅርጽ እየቀረጹ ይሰግዱላቸው ነበር ።

እንደዚሁም የፊንቂ ሰዎች ራሳቸው የሚከተሉት የተለየ አምልኮ ፣ነበራቸው ነገር ግን ከግብጾች ጋር ብዙ ግንኙነት ስለነበራቸው አምልኮአቸውና የአምልኮታቸው መልክና ስም ከግብጾች ጋር የሚገጣጠም ነበር ። ስለዚህም እንደ ግብጾች አምልኮት የፊንቂዎችም አማልክት የተለያዩ ስሞች ነበራቸው ፣ከብዙዎችም አስማት መካከል ኤል ፣በዓል ፣ምሉክ የሚባሉ ይገኛሉ ።

የእነዚህም አማልክት መቀመጫቸው በተራራዎች ላይ ነው የሚል አስተሳሰብ በአምላኪዎች ሕዝቦች ዘንድ ነበር። እንደ ስማቸው ለአማልክቱ የሚቀርቡላቸውም መሥዋዕቶች የተለያዩ ናቸው ለምሉክ የሚቀርበው መሥዋዕት እንደሌሎቹ አማልክት ከብት ሳይሆን ወንድ ወይም ሴት ልጅ ነበር ።

በብሉይ ኪዳን ተጽፎ እንደምናነበው ሞሳ የሚባለው የሞአብ ንጉሥ ከእስራኤላውያን ንጉሥ ከኢዮራምና ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮሳፍጥ ጋር ተዋግቶ ቢሸነፍ ድል የሆንኩት አምላኬ ባይረዳኝ ነው አለና በእግሩ ተተክቶ መንግሥቱን ሊወርስ የሚገባውን የበኩር ልጁን ወስዶ ለከንቱ አምልኮ ሲል ሠውቶ ለሚቃጠል መሥዋዕት በቅጥሩ ላይ አቀረበው ፣ ቢሆንም “በእሥራኤልም ዘንድ ታላቅ ቁጣ ሆነ ከዚያም ርቀው ወደ ምድራቸው ተመለሱ” ይላል እንጂ ልጁን አርዶ መሥዋዕት ያቀረበለት ጣዖት ረድቶ ድልን እንዲያገኝ አደረገው አይልም ።

ሁለተኛ ነገሥት ፫. ፳፯

ከዚያ ሲያያዝ በመጣው ልማድ ይመስላል በእኛም ሀገር ቀደም ሲል የነገሥታቱ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ምጥ ሲይዛቸውና ሲጠናባቸው ፣እንዲሁም ነገሥታቱ ትልቅ ሐውክ የገጠማቸው እንደሆነ አስማተኞች ጠንቋዮችን ጠይቀው አንድ ቀለሙና መልኩ ያማረ ኮርማ አሳርደው ይጥሉ ነበር የሚባለው።

ሁሉም ዓለም በየሀገሩ ልዩ ልዩ አምልኮትና ልምድን እየፈጠረ ሲጓዝ ኑሯል ፣በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገሮች በልብ ወለድ የተፈጠረው አምልኮም ሆነ የአምልኮ ሥርዓት ቢበዛም ቢያንስም እርስ በርሱ የተቀራረበና የተመሳሰለ ሆኖ ይገኛል ። ቢሆንም ቀዳሚውና ተቀዳሚው ፣ሰጭውና ተቀባዩ ፣መምህሩና ተማሪው ማንኛውም ወገን መሆኑን ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው ።

ለምሳሌ በሀገራችን የከብቱን ሞራ እየተመለከቱ የሚጠነቁሉ እንዳሉ በሮማውያንም ለመሥዋዕት የሚታረደውን ከብት ሆድ ዕቃ ውስጥ ያለውን እየመረመሩ እንዲሁም መሥዋዕቱ ሲቃጠል የጢሱን አካሄድ እየተመለከቱ ስለ ክፉና ደግ ነገር የሚተነብዩ መኖራቸው ይነገራል ።

ሌሎች ክፍሎች ደግሞ የምድር አራዊትንና የሰማይ አዕዋፍን አበራረርና አጯጯህ እየተመለከቱና እያዳመጡ በተጨማሪም የሰማይ ከዋክብትን፣ጨረቃን ፣የፀሐይ ሁኔታ እየተመለከቱ በዚህ ዘመን ረኃብ ፣በዚህ ዘመን ጥጋብ በዚህ ዘመን አባር ቸነፈር በዚህ ዘመን ጦርነት በዚህ ዘመን ሰላም ወዘተ ይሆናል እያሉ የሚናገሩ አሉ ።

ከንቱ አምልኮ በማንኛውም ሀገር በማንኛውም ጊዜ የሚፈጸም መሆኑ ቢታወቅም በይበልጥ በወርኃ ግንቦት በርከት ያሉ አምልኮቶች በልዩ ልዩ መንገድ እንደሚፈጸሙ ከላይ ተጠቅሷል ።

ነገር ግን ከአንድ እግዚአብሔር በስተቀር ሌላ ሊያድን የሚችል አምላክ ስለሌለ በግንቦት ወርምሆነ በሌላ ጊዜየሚፈጸም አምልኮ ባዕድ ሁሉ ለሥጋም ሆነ ለነፍስ የማይበጅ ከንቱ መሆኑን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከማስተማር ተቆጥባ አታውቅም ።

በአሁኑ ጊዜ ኅብረተሰቡ ሊዘምትባቸውና ሊያስወግዳቸው ከሚገቡት ነገሮች አንዱ ከንቱ አምልኮ ነውና ሁሉም ሰው ለዚህ ተግባር የመተባበር ግዴታ አለበት ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

# ሰዎችና መላእክት እያዩት ....

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ሲገዙለትም የሚኖሩ መሆናቸውን የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ብሎአል።“ዐርገ በስብሐት ፣ ውስተ ሰማያት ፣ ተኮነኑ ሎቱ መላእክት ኵሉ ኃይል ፣ ወኵሉ ፍጥረት” በታላቅ ምስጋና ዐረገ ፣ መላእክት ኃይል ሁሉ ፣ ፈጥረታትም ሁሉ ተገዙለት፣ (ድጓ) ይህ የሚያመለክተው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ገዥ የዘለዓለም አምላክ መሆኑን እርሱም በድል አድራጊነት ወደቀደመ ክብሩ ያረገ መሆኑን ነው ።

የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት የሚያመለክተው ክርስቲያኖች በክብር ወደ ሰማይ የሚያርጉ መሆናቸውን ጭምር ነው ።

ስለዚህ የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት የክርስቲያኖች ክብርና ደስታ ፣ ደኅንነትም በመሆኑ ማንኛውም ክርስቲያን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የዕርገቱን መታሰቢያ በዓል በታላቅ ደስታና ክብር በተመስጦም በየዓመቱ ያከብረዋል ።

የክርስቶስ ዕርገት ለሁሉም ግልጥ ሊሆን ያስፈልጋል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በመንፈስ የፀደቀ ፣ ለመላእክት የታየ ፣ በአህዛብ የተሰበከ ፣ በዓለም የታመነ ፣ በክብር ያረገ ፣ እርሱ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ፩ኛ. ጢሞ. ፫፤፲፮ ።

ተስፋ ጥሩነህ

# ቤተክርስቲያንና...

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ለምሳሌ የኢትዮጵያ ን ታሪክ ለሚመረምር በ፲፱ኛ ክፍለ ዘመን የአፍሪካ ዕድል በባእዳን እጅ ሲወድቅ ኢትዮጵያውያን የነፃነት ሸማን ተጎናፅፈው ኖረዋል።ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ የጦር መሣሪያ ኖሮት ሳይሆን ፣የፍትሕን ፣የነፃነትንና የእኩልነትን ትርጉም የተረዳ በመሆኑለመብቱና ነፃነቱ ሕይወቱን እየሠዋ ኖሮአል ። ለዚህም መሪና አስተማሪ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሆነች የታሪክ ሐቅ ነው ።





www.ethiopianorthodox.org

## የመጀመሪያው የሙሴ ጽላት ሰባሪ ተገኘ

ሙሴ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ ነው ። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መሥክሮለታል ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡ ለማንም ቢሆን በሕልም ወይም በራእይ እገለጽለታለሁ ። ሙሴን ባሪያየን ግን ቃል ለቃል አነጋግረዋለሁ ሙሴ በቤቴ የታመነ ነውና ይላል የመጽሐፍ ቅዱስ መሥራችና በመጀመሪያም አሥርቱ ቃላትን ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበለ ሙሴ ነው ።

ይህ ቅዱስ ሰው ለእስራኤላውያንም ከባርነት ቀምበር ነፃ መውጣት በእሱ አማካይነት በመሆኑ ለብዙ ዘመን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ በኋላ ተራራ እስከ ተቀበረበት ቀን ድረስ ከግብፅ የወጡትን ሕዝቦች የመራና በሕግ ያስተዳደረ ጥሩ መሪ ነበር ።

ሙሴ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት በመሆኑ ትዕግሥተኛና ብልህ ሕጋዊ ሰው መሆኑ ይነገርለታል ። አስተዳደጉም በግብፅ ነገሥታት ቤት በመሆኑ ሥርዓት አዋቂና ጠንቃቃነቱም ታውቆለታል ።

በዚህ ምክንያት እስራኤላውያን ሙሴን ይፈሩትና ይወዱትም ነበር ። በሞተም ጊዜ ከሞተበት ቀን ጀምሮ እስከ ሠላሣ ወይም እስከ አርባ ቀን ማያቋርጡ ግልቀሣቸው ተጽፎ ይገኛል ።

ይህ ታሪካዊ ሰው ገርማው የሚያስፈራ የእግዚአብሔርን ፀጋ የተሞላ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር በሙሴ አድሮ በሙሴ እጅ የተለያዩ ድንቅና ግሩም የሆኑ ተአምራቶች ተከናውነዋል ።

ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በሙሴ የተደረገውን ተአምራት እንደሙሴ ያደረገ የለም ። ሙሴ ከጨካኝ ገዥ ከፈርዖን እጅ እስራኤላውያንን ነፃ በማውጣቱ ኋላ ዓለምንና የሰው ልጆችን ከጨካኙ ከዲያብሎስ እጅ ነፃ ለማውጣት ለመጣው ለጌታችን በምሳሌነት ይጠቀሣል ።

ይህ ነቢይ ከባለሟልነቱ ብዛት የተነሣ እግዚአብሔርን መልኩን ለማየት ጠየቀ ነገር ግን እግዚአብሔርም የሱን ፊት ለማየት እንደማይችል ከነገረው በኋላ ወደሲና ተራራ እንዲወጣ ከዚያም የሕጉቹን ፅላቶች እንዲቀበል አዘዘው ። ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደ ተራራ ወጣ ከዚያም ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገርና ሕጉንም ሲቀበል ፵ ቀን ቆየ ። እስራኤላውያንም በአሮንና በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ ። እንዲህም ብለው አሮንን የሙሴን ወንድም አስጨነቁት ። ሙሴ የሄደበትን ሄዶም እግዚአብሔር ያደረገውን አናውቅምና ። የምንሰግድበትና የምናመልክበት ነገር ይሠራልን ብለው አስቸገሩት ። አሮንም በነገራቸው ተቸገረ ። የሕዝቦቹን ፈቃድ ለመፈጸም የሚያመልኩበት ጣዖት ይሠራ ብሎ በጥያቄያቸው ቢስማማ ከፈጣሪው የሚጣላ መሆኑን ተገነዘበ ።

አይሆንም አይሠራም ከእግዚአብሔር ሌላ ለባዕድ አምላክና ለጣዖት መስገድ ክልክል ነው ብሎ እንዳይከለክል ሰይጣን ያገበራቸው ሰዎች ተባብረው ይገድሉኛል ሲል ፈራ ።

ወንድሙ ሙሴ እስኪመጣ ነገሩን ለማዘግየት አሰበ የእስራኤላውያንን ወርቅ ወዳድነት ስለሚያውቅ የያዛችሁትንና ያላችሁን ወርቅ አምጡና የወርቅ ጥጃ ይሠራላችሁ አላቸው እነሱም ጥቂት እንኳ ሳያንገራግሩ የጣት ቀለበታቸውን የጆሮ ጉትቻቸውን አውልቀው አመጡለት ። አሮንም በጥጃ ምስል አሠራው እግዚአብሔርም ሙሴን ሂድ ወደዚያ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ውረድ የሚያደርገውንም እይ እኔን አሳዝነውኛልና አለው ። ሙሴም የሕጎችን ጽላት እንደያዘ ሲወርድ ከወርቅ ለተሠራው ጥጃ ሲሰግዱ አያቸው ለአምላኩ ሕግ ቀናዒ ከመሆኑና ከቁጣ ብዛት የተነሣ ትዕግሥቱ ከእሱ ራቀ በእጁ የያዛቸውንም ፅላቶች ወረወራቸው ጽላቶቹም ተሰበሩ ።

ሙሴም ያንን የወርቅ ጥጃ አስፈጭቶ አጠጣቸው በዚህ ክፉ ምክር የተባበሩ እስራኤላውያን ሁሉ ያንን የተፈጨ ወርቅ እየጠጡ በእባጭና በበሽታ በልዩ ልዩ ደዌ አለቁ ።

ሙሴም ከእስራኤላውያን መሀከል ክፉዎችን ካስወገደ በኋላ ሌላ የሕግ ፅላት እንዲሰጠው እግዚአብሔርን ጠየቀ እግዚአብሔርም ሙሴን ራስህ እንደ መጀመሪያዎቹ አድርገህ ቅረጽ አለው። ሙሴም የሕግ ገበቶቹን ቀርፆ ለእግዚአብሔር አቀረበ እግዚአብሔርም አድርግና አታድርግ የሚሉትን አርእስተ ሕጎች በጽላቱ ላይ ጻፈለት ያም የተሰበረው ጽላት በዚያው በተሠበረበት በሲና ተራራ ግርጌ ወድቆ በመቅረቱ ለብዙ ዘመናት አቧራና ትቢያ ተከምሮበት ሲኖር በአሁኑ አርኪዮሎጂስቶች ምርምርና ቁፋሮ ብዙ ድካም ካስከተለ በኋላ በሲና ተራራ በስተሰሜን በኩል ተገኘ የተገኘውም የፅላት ስባሪ ፅላቱ የተቀረፀው ከጥሩ ዐይነት እብነ በረድ ነው። በላዩም የተጻፈው በሁለት ፊደሎች ነው በአንድ በኩል በእብራይስጥ በአረማይክ ፊደልና ቋንቋ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በዮናናውያን ፊደልና ቋንቋ ነው በላዩም የተጻፈው ጽሕፈት እንደ ጥንቱ የፊደል አጣጣልና አጻጻፍ ሳይሆን በመሀከለኛው ዘመን ሥልጣኔ በተስፋፋበት ጊዜ የተጻፈ ወይም በመኪና የተቀረጸ ሥነ ጽሑፍ ይመስላል ። በመሀከሉም የመስቀል ምልክት ስለአለበት ወደፊት ለቤዛነት የተሰቀለውን የጌታችን መስቀል ያበሥራል ።

ናሽናል ጂኦግራፊ ከተባለው እንግሊዝኛ መጽሔት ቅጽ ፻፵፱ ቁ. ፩ ጥር ፲፱፻፸፮ እ.ኤ.አ. ተተረጐመ ።



## ልደታ ለማርያም

ከዙ ፲ የዞረ

ከዚኽም የተነሣ ልጅ ያጡ ሰዎች ሁሉ ልጅ እንዲሰጣቸው አዘውትረው ወደ እግዚአብሔር ሲለምኑ የኖሩ በርከት ያሉ ናቸው ልጅ አጥተው ልመናቸውን ወደ እግዚአብሔር ሲያስተጋቡ ከኖሩ ሰዎችም መካከል ኢያቄምና ሐና ይገኙባቸዋል ኢያቄምና ሐና በሕግ ተጋብተው ሲኖሩ በወቅቱ ልጅ ባለመውለዳቸው ከባድ ሐዘን ሳይሰማቸው አልቀረም ሆኖም ልጅ እንዲሰጣቸው ጥዋት ማታ እግዚአብሔርን ከመለመን ተስፋ ባለመቁረጥ ወደ ቤተ እግዚአብሔር እየሄዱ ከመጸለይ ያቋረጡበት ጊዜ ከቶ እንዳልነበረ ታሪክ ያስታውሳል በዚህ ዓይነት ብዙ ዘመናት ካሳለፉ በኋላ ወደ እርሱ አምነው ለሚቀርቡ እግዚአብሔር ቅርብ ነውና ጸሎታቸውን ሰምቶ ልመናቸውንም ተቀብሎ ሀሳባቸውን እንደሚያሟላላቸው አምነው በመጨረሻ ስለት ተሳሉ ኢያቄምና ሐና ስለት ሲሳሉ ልጅ እንዲሰጣቸው ብቻ አልነበረም የሚወልዱትም ልጅ በእግዚአብሔር አምልኮት ጸንቶ የሚኖር ሰውን የማያስቀይም ፈጣሪውንም የማያሳዝን እንዲሆንላቸው ሐሳባቸውንና ስለታቸውን ለይተው ተስለዋል ከዚህም በላይ ልጅ ከሰጠን ወንድ የሆነ እንደሆነ እርስህ ቆፍረህ እርዳን አንለውም ቤተ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ሴት ልጅ የወለድን እንደሆነ ደግሞ ውኃ ቀድተሽ እንጨት ሰብረሽ እርጅን አንላትም ለቤት እግዚአብሔር አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች እየሠራች እንድትኖር ለቤተ እግዚአብሔር እንሰጣታለን ብለው ተሳሉ እነዚህ ቅዱሳን ሁለቱም ተስማምተው ተስለው ወደ ቤታቸው ከሄዱ በኋላ አንድ አስደናቂ የሆነ ራእይ አዩ የሁለቱም ራእይ የተለያየ ነበር ይኸውም ሐና ያየችውን ራዕይ ለኢያቄም ስትነግረው ያማረ ገምጃ ስትታጠቅ መቋምያህም ለምልማ አብባና አፍርታ ፍሬዋን በዓለም ያለው ፍጡር ሲመገባት አይቻለሁ ስትል ነገረችው ይህንን ከሐና ከሰማ በኋላ ኢያቄምም ያየውን ራእይ ለሐና እንዲህ ሲል ነገራት እኔምኮ ራእይ አይቻለሁ አንዲት ነጭ ርግብ ሰባቱን ሰማያት ሰንጥቃ ወርዳ በራስሽ ላይ ስታርፍ አይቻለሁ ሲል ያየውን ራእይ ነገራት እግዚአብሔርም በረድኤት ጎበኛቸውና ነሐሴ 7 ቀን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተጸንሳለች በተጸነሰችም ጊዜ በእናትዋ ማህፀን ሳለች ድንቅ ሥራዎችን ተአምራትን በማሳየት ብዙ ድውያን አድናለች እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ግንቦት 1 ቀን ተወለደች የቤተ ክርስቲያን ሊቅ አባ ሕርያቆስም "ድንግል ሆይ በኃጢአት ፍትወት የተጸነስሽ አይደለም በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐናና ከኢያቄም ተወለድሽ እንጂ ብሏል ቅዳ ማር. ቁ. ፴፰ ።

ሐናና ኢያቄም ልጅ ሳይወልዱ በእንባ ይታጠቡ ነበር ልጅ ከወለዱ በኋላ ግን እንባቸው ደርቆላቸዋል ። እሁንም ቢሆን በእርስዋ አማላጅነት የሚያምኑ በክርስቶስ አዳኝነት የሚማፀኑ ሁሉ ጽኑዕ ሐዘን እንደማያገኛቸው እናምናለን የኢያቄምና የሐና ሐዘን እመቤታችንን በመውለድ ሐዘናቸው እንደ ተረሳ በአዳም የተፈረደውም ፍዳ ኃጢአት በእመቤታችን አማላጅነትና ከእርስዋ በተወለደውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት ስለ ጠፉ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ አይኖርም ስለዚህ በእመቤታችን ልደት ደስታ ለኢያቄምና ለሐና ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ ነው ።

ከንፈ ርግብ ማርቆስ

## ፍልሰተ አጽሙ ለተክለሃይማኖት

ከዙ ፲፱ የዞረ

ውስጥ ሐር ከሚባለው ሥፍራ ነው ። እነዚህም ብፁዓን አባቶች ኢትዮጵያን እንደ ከዋክብት በወንጌል ትምህርት ያበሩና ያስጌጡ መምህራን (እጨጌዎች) ናቸው ።

ይህም ገዳም ታችኛው ገዳም ኮራ ላይኛው ደብረ ዓሰቦ ገዳመ ዓሰቦ እየተባለ እስከ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ድረስ ከቆዩ በኋላ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በ፲፬፻፴፭ ዓ.ም. ገዳማ ደብረ ሊባኖስ ተብሎ ተሠየመ ይባላል። ዓ.ምሕረቱን ፳፭ የሚሉም አሉ ። ይሁን እንጂ ወደ ፍሬ ነገራችን እንመለስና ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት መታሰቢያ በዓመት ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸው ፫ በዓላት አሉ ። እነዚሁም ፩ኛ ታሕሣሥ ፳፬ ቀን በ፲፩፻፺፯ ዓ.ም. የተወለዱበት ነው ። ፪/ኛ ነሐሴ ፳፬ ቀን በ፲፪፻፺፯ ዓ.ም. ያረፉበት ነው ። ፫ኛ/ ፍልሰተ ዓፅማቸው በ፲፫፻፶፯ ዓ.ም. ግንቦት ፲፪ ቀን ነው ። ይህንንም አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች በመቃወምና በቁጥሩ ባለመስማማት የተወለዱበትን በ፲፩፻፶፪ ይላሉ ። ያረፉበትን ደግሞ በ፲፪፻፷፮ ሲሉ ፍልሰተ ዓፅማቸውንም በ፲፫፻፶፫ ይላሉ ።፪ተኛ ስለ ፍልሰተ ዓፅማቸው ገድሉ እንደሚናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕለታት አንድ ቀን በራዕይ ተገልጦ ይህች ዋሻህ ፈርሳ ዓፅምህን አውጥተው አሁን ካለበት ቦታ የሚቀበር መሆኑን ለተክለ ሃይማኖት ነገሯቸው ነበር ። ልክ በተቀበሩ በ፶፯ ዓመት በእጨጌ ሕዝቅያስ ዘመን ፲፪ቱ ንቡራነ እድ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ከየሀገረ ስብከታቸው ተሰብስበው መጥተው ግንቦት ፲፪ ቀን ዓፅማቸውን አፍልሰው አውጥተው ጌታ እንደተናገረው አሁን ካለበት ቦታ ቀብረዋቸዋል ። መጀመሪያ የተቀበሩት ደብረ ዓሰቦ ሲሆን ዓፅማቸውም የፈለሰው ከደብረ ዓሰቦ ወደ ደብረ ኢላም ነው ዔላምም የሚባለው አሁን ደብረ ሊባኖስ እየተባለ የሚጠራው ነው ። ስለዚህ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት በየዓመቱ ግንቦት ፲፪ ቀን የሚከበርበት ምክንያቱ ፍልሰተ ዓፅማቸውን ለማሰብና ለማስታወስ ነውና።እኛም ከዚህ ዓለም ፈልሰን በሞት ተለይተን ከመሐዳችን አስቀድመን ንስሐ ገብተን ከኃጢአት ርቀን ለጽድቅ የሚያበቃ ሥራ ሠርተን ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ብሎ ጌታችን እንዳስጠነቀቀን ሁሉ ዕድሜ ለንስሐ ዘመን ለፍሥሐ እንዲሰጠን እንለምነው።

አባ ቸርነት ጋሻው በዛ



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ

# የግዕዝ ትምህርት

## ትምህርት 6

| | | | |
|---|---|---|---|
| እድ | እጅ | ላዕለ | በ-ላይ |
| ምስለ | ከ-ጋር | ዲበ | በ-ላይ |
| ኀበ | ወደ | ድህረ | በ-ኋላ |
| ቅድመ | በ-ፊት | እንበለ | ያለ በቀር |
| ህየንተ | ስለ ፈንታ | እም | ከ |
| መንገለ | በኩል ወደ | እምነ | » |

መከሥት፡- ከዚህ በላይ ያጠናናቸውን ቃላት ለማርባት ስንፈልግ መድረሻ ፊደላቸውን ወደ ሐምስ እንለውጣለን ። ለምሳሌ አከሥት በምሳሌ " ምስለ" "ኀበ" የተሰኙትን ቃላት አሁን እናርባ።

ሀ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምስሌየ | ከእኔ ጋር | ምስሌነ | ከእኛ ጋር |
| ምስሌከ | ከአንተ ጋር | ምስሌክሙ /ተባ/ | ከእናንተ ጋር |
| ምስሌኪ | ከአንቺ ጋር | ምስሌክን አን | ከእናንተ ጋር |
| ምስሌሁ | ከእርሱ ጋር | ምስሌሆሙ /ተባ/ | ከእነርሱ ጋር |
| ምስሌሃ | ከእርስዋ ጋር | ምስሌሆን አን | ። |

ለ " ኀበ" የሚለውን ደግሞ ልክ እንደዚሁ ለማርባት እንሞክር

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀቤየ | ወደእኔ | ኀቤነ | ወደእኛ |
| ኀቤከ | ወደአንተ | ኀቤክሙ /ተባ/ | ወደእናንተ |
| ኀቤኪ | ወዳንቺ | ኀቤክን /አን/ | ወደእናንተ |
| ኀቤሁ | ወደእርሱ | ኀቤሆሙ /ተባ/ | ወደ እነርሱ |
| ኀቤሃ | ወደርስዋ | ኀቤሆን /አን/ | ወደ እነርሱ |

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ዐረፍተ ነገር ለመሥራት እንድንችል የሚከተሉትን ቃላት እናጥና ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሥያጥ | ገበያ | ንዑ /ተባ/ | ኑ |
| እም | እናት | ነዓ /አን/ | " " |
| ነዐ | ና | ቀረብ | መቅረብ |
| ሐዊር | መሄድ | መጺእ | መምጣት |
| ንዒ | ነይ | ላእክ | መልእክተኛ /ተላላኪ |
| | | በጺሕ | መድረስ |

## ዐረፍተ ነገር

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዮሐንስ ሖረ ምስለ መስፍን | ዮሐንስ ከመስፍን ጋር ሄደ | ፍቁርኪ መጽአ ኀቤኪ | ወዳጅሽ ወዳንቺ መጣ |
| እምየ ሖረት ኀበ ምሥያጥ | እናቴ ወደ ገበያ ሄደች | ሖረ ኀቤሁ | ወደርሱ ሄደ |
| እኁየ ነዐ ኀቤየ | ወንድሜ ወደ እኔ ና | ቀርበ ኀቤሃ | ወደርስዋ ቀረበ |
| እኅትየ ንዒ ኀቤየ | እቴ ወደ እኔ ነይ | ወልድየ መጽአ ኀቤክሙ/ተባ/ | ልጄ ወደናንተ መጣ |
| አኃዊነ ንዑ ኀቤነ | ወንድሞቻችን ወደእኛ ኑ | መጽአ ላእክ ኀቤክን/አን/ | መልእክተኛው ወደ እናንተ መጣ |
| አኃቲነ ነዓ ኀቤነ | እቶቻችን ወደእኛ ኑ | ሖረ ላእክ ኀቤሆሙ | መልእክተኛው/ተላላኪው/ ወደ እነርሱ ሄደ ። |
| እኁከ መጽአ ኀቤከ | ወንድምህ ወደ እናንተ መጣ | በጽሐ ላእክ ኀቤሆን /አን/ | መልእክተኛ ወደ እነርሱ ደረሰ |

"ድህረ ፣እንበለ ፣እምነ ፣ህየንተ የተባሉትን ቃላት ኀበ እና ምስለን" ባረባችሁበት መንገድ እርቡ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማኅበረ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቁ. 116616
የመል. ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ